ግንቦት 9 ቀን 2008 ዓ.ም

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች

2007 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት

የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት

የተከበሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀፅ 2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 18 እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተሰጠው ስልጣን መሠረት መ/ቤቱ ኦዲት ያደረገውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ (Protection of Basic Services) ፕሮግራም አማካይነት የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሰጠውን የበጀት ድጋፍና ድጎማ ተከታታይ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች፤ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ህጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ፤ ተፈላጊውን ግብ የመታና ውጤት ያስገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገውን የክዋኔና አካባቢ ኦዲት፣ እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ በተደነገገው መሠረት የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትና በተመረጡ የፌዴራል

መንግሥት መ/ቤቶች ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲቶች ዕቅድ ክንውንና የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፤

1. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት እና በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮግራም ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍ (Protection of Basic Services III) ተከታታይ እና የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች ናቸው፤

2. ሪፖርቱ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት የተደረጉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሂሳብና በልማት አጋር ድርጅቶች እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞችን ኦዲት ያካትታል፡፡

3. የ2007/8 ኦዲት ዓመት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድ ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን አጭር የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃለለ ነው፡፡

4. የ2007 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች፣ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው 6 መ/ቤቶችና የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው 36 መ/ቤቶች፣ እንዲሁም የ18 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችና የ4 ክዋኔ ኦዲት የክትትል ኦዲት ለም/ቤቱ የቀረቡ ስለሆነ፣ እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡ የሪፖርቶቹም ቅጅ ሶፍት ኮፒና የተጠቃለለው በ2 ጥራዞች /የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርትና አጠቃላይ ዘገባ/ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤትም እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

5. እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ስብሰባ (Exit Conference) ከመደረጉም ሌላ ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል፡፡

6. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዓለም አቀፍ የመንግሥት የኦዲት ደረጃዎች፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ሲሆኑ፣ ኦዲቱም የተከናወነው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

<u>የ2007 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ኦዲት ዕቅድና ክንውን</u>

<u>የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ</u>

7. የ2007 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ የኦዲት ዕቅዳችን መሠረት ያደረገው እንደተለመደው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናትንና የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 አንቀጽ 63/2 መሠረት የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ሂሳባቸውን በመዝጋት ለኦዲት ማቅረብ እንዳለባቸው በተደነገገው መሠረትና በሌላም በኩል መ/ቤታችንም በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች ሂሳባቸውን ዘግተው ሲያቀርቡ ኦዲቱን በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ማለትም እስከ ታህሣሥ 30 በማጠናቀቅ ሪፖርቱን ለኦዲት ተደራጊዎች ለመስጠት ግብ ጥሏል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችለው የኦዲት ካላንደርና ዘዴ ላይ ለውጥ በማድረግ ኦዲቱ የሂሳብ መዝጋትን ሳይጠብቅ በየዓመቱ በጥር ወር ተጀምሮ በተከታዩ ዓመት ታህሣሥ ላይ የሚጠናቀቅበት ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉ ይታወሳል፡፡ ሆኖም በ2006 በተደረገው ኦዲት በርካታ መ/ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት

መስከረም 30 የሂሳብ መግለጫዎቹን አዘጋጅተው ለኦዲት ባለማቅረባቸውና ሥራውም በሠራተኛ ፍልሰት ምክንያት እየገፋ በመሄዱ የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ መጋቢት 1 ቀን 2007 ተጀምሮ ጥር 30 ቀን 2008 ለማጠናቀቅ ነበር የታቀደው፡፡

8. በዚሁ መሠረት በ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 153 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል 145 መ/ቤቶችን ከ24 ቅ/ጽ/ቤቶች ጋር በመ/ቤታችን፣ የተቀሩትን ስምንቱን ደግሞ በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሽፋኑን 100% ለማድረስ የታቀደ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመ/ቤታችን በኩል ኦዲት ለማድረግ ከታቀዱት 145 መ/ቤቶች የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ የሁሉም ኦዲት (ከ23 ቅ/ጽ/ቤቶች ጋር) የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የ2007 በጀት ዓመት የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት በመከናወኑ የፋይናንስና ህጋዊነት የአፈጻጸማችን 100.00% ለማድረስ ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኦዲት ዘግይቶ በመጠናቀቁና ለሥራ አመራር ሪፖርቱ ምላሽ ተሰጥቶ የመውጫ ስብሰባ ባለመደረጉ ግኝቶቹን በዚህ ሪፖርት ውስጥ ለማካተት አልተቻለም፡፡

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች

9. የ2007 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን በ145 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች እና በ294 የወረዳና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን፣ ሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር ከ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ /የተሰጠው የኦዲት አስተያየት/	በፌዴራል መንግሥት ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲት		አጠቃላይ	
	2006	2007	2006	2007	2006	2007
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት	39	36	1		40	36
ከጥቅት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው የተገኙ	63	66	299	294	362	360
አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች	11	6			11	6
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	20	37			20	36
ድምር	**134**	**145**	**300**	**294**	**434**	**439**

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች

10. መ/ቤታችን ምክር ቤቱ ያጸደቀው በጀት የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ፣ ደንብና መመሪያ በሚፈቅድው መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ ባከናወነው ኦዲት በርካታ የሂሳብ አያያዝ ግድፈቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከደንብና መመሪያ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች የተገኙ ሲሆን፤ የም/ቤቱን ትኩረት ሊያገኙ ይገባል ተብሎ የታመነባቸው አንኳር ግኝቶች ብቻ ተለይተው እንደሚከተለው ቀርቧል::

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

11. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝና አጠባበቅ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ3 መ/ቤቶች ብር 196,544.65 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተገኘባቸውም የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ እና የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ ናቸው፡፡

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በ6 መ/ቤቶች (ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ አሶሳ ዩኒቨርስቲ፣ ሀሮማያ ዩኒቨርስቲ፣ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ግብርና ኮሌጅ፣ በፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ እና በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር-በስልጠና ዋና መምሪያ) ቆጠራው በብር 284,971.53 በማነስ ልዩነት የታየ ሲሆን፣ በ6 መ/ቤቶች (ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ፣ ሀሮማያ ዩኒቨርስቲ፣ ሚዛን ቴፒ፣ ወሎ ዩኒቨርሲቲ እና በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር - በሎጅስቲክ ዋና መምሪያ) ደግሞ ብር 2,034,074.93 ቆጠራው ከመዝገብ በመብለጥ ታይቷል፡፡ እንዲሁም በ28 መ/ቤቶችና በ5 ቅ/ጽ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች መኖራቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

12. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳቦች ላይ ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ብክነት፣ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፣ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፣ በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በቆጠራ ከተገኘው ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ፣ በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተገቢው እርምጃ ተወስዶ እንዲተካ፣ በማነስ/በመብለጥ የታየው ልዩነትም ተጣርቶ እንዲተካ ወይም ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ እና የታዩት የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዲስተካከሉ አሳስበናል፡፡

የውዝፍ ተሰባሳቢ ሂሣብ

13. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳዳር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 በተደነገገው መሠረት የሰነድ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ

ሲጣራ በ94 መ/ቤቶችና በ11 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር **2,078,949,440.60** በደንቡ መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

14. ከዚህ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 342,235,704.80፣ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 315,133,460.41፣ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ብር 172,191,236.99፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 139,258,386.16፣ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 138,482,895.82፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 85,982,359.92፣ የግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጠና ማስተባበሪያ ብር 75,882,513.81፣ ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 69,010,479.00፣ እና በገ/ጉ/ባለሥልጣን የአዲስ አበባ ኤርፖርት ብር 67,228,586.69 ይገኙበታል፡፡

15. ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣቡ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት በወቅቱ ካልተወራረደ ወይም ካልተሰበሰበ በቆየ ቁጥር የመሰበሰብና ወደ ሀብትነት የመለወጥ እድሉ ተዳክሞ ባክኖ የሚቀር በመሆኑ መ/ቤቶቹ የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው ገንዘቡን እንዲሰበስቡ ወይም እንዲያወራርዱ አሳስበናል፡፡

በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ዋና ዋና የአሠራር ችግሮች

16. የተሰብሳብ ሂሳብ አያያዝ የፋይናንስ ደንቡን የተከተለ መሆኑ ሲጣራ የሚከተሉት የአሰራር ችግሮች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡

- በ4 መ/ቤቶች የተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀፅላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ሂሳብ ብር 174,023,890.94 መገኘቱ፣
- በ9 መ/ቤቶችና በ1 ቅ/ጽ/ቤት ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ሚዛን (Abnormal balance) ብር 58,521,861.28 የሚታይባቸው መሆኑ፣
- በ2 መ/ቤት እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 48,100,306.61 ማስረጃ ሊቀርብለት ስላልቻለ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣
- በ2 መ/ቤቶች በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው አላግባብ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘ ብር 15,944,606.97 መገኘቱ፣

- በ4 መ/ቤቶች በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተገኘባቸው ብር 17,615,101.49 መገኘቱ፤
- በ1 መ/ቤት በማነስ ሪፖርት የተደረገ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 8,813,345.26 እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ብር 67,387,848.40 ተሰብሳቢ ሂሳብ መገኘቱ

በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

17. በመሆኑም አላአግባብ በተሰብሳቢ የተመዘገበው ሂሳብ እንዲስተካከል፣ ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግላቸው፣ ተቀፅላ ሌጀር የሌላቸው እንዲመሠረትላቸው፣ ማስረጃ የሌላቸው ማስረጃ ተሟልቶላቸው እንዲያዙ እና ለወደፊቱ ባልተሟላ ማስረጃ የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት እንዳይዘጋጅ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የገቢ ሂሣብ</u>

18. የመንግሥት ገቢ በወጡት ሕጎች መሰረት በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝቷል፡፡

<u>በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ</u>

19. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ34 መ/ቤቶች እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ አስራ አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 118,705,272.89 እና በ1 መ/ቤት ተማሪዎች በገቡት ውል መሠረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ያልተሰበሰበ USD 211,930.00 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

20. በአዋጁ መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 38,247,446.01፣ የአዲስ

አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ብር 27,938,793.13፣ መቀሌ ቅ/ፅ/ቤት፤ 18,246,561.67፣ ኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት ብር 8,034,322.15፣ አዳማ ቅ/ፅ/ቤት 7,328,092.67፣ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,267,580.75፣ በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,131,240.28 እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብር 2,332,802.70 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

21. የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ ሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Custom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በትክክለኛው የትራንስፖርት የመጫኛ፣ ማራገፊያና ኢንሹራንስና ሌሎች ወጪዎች ለቀረጥ ማስከፈያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር፣ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች ላይ በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ ያለፈበት ቢሆንም በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ በመሆኑ እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

22. በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥትን ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

መሰብሰብ ሲገባ ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሣ ሂሳብ

23. በፌዴራል መንግሥት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4 (ሀ) እና (ለ) መሠረት አቅራቢው ሣይፈጽም በቀረው የውል መጠን ላይ ውል ሰጪ የመንግሥት መ/ቤቶች በየቀኑ 1% ወይም 1/1000ኛ ከውሉ ዋጋ

10% ሣይበልጥ የጉዳት ካሣ ሊሰበስቡ እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ በዚህ መሠረት መ/ቤቶች በውሉ መሠረት ባልፈጸሙት አቅራቢዎች ወይም አገልግሎት ሰጪዎች ላይ በመመሪያው መሠረት ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑ ሲጣራ በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ያልተሰበሰብ የጉዳት ካሣ ወይም ቅጣት ከስራ ተቋራጮች በ13 መ/ቤቶች ብር 497,970,406.59 እና ከዕቃ አቅራቢዎች በ6 መ/ቤቶች ብር 3,267,830.99 በድምሩ ብር 501,238,237.58 ተገኝቷል፡፡ የጉዳት ካሣውን ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 147,652,432.00፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 135,762,545.48፣ አሶሳ ዩኒቨርስቲ ብር 53,573,621.00፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 35,451,234.64 እና ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ብር 33,570,438.40 ናቸው፡፡

24. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በተቀመጠው መመሪያ መሠረት እስከ አሁን ያልተሰበሰበውን የጉዳት ካሣ እንዲሰበስቡና ለወደፊቱም መመሪያው በሚጠይቀው መሠረት እንደፈጽሙ አሳስበናል፡፡

ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

25. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በአንድ መ/ቤትና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንና በስሩ ባሉ አስራ አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር 205,113,732.24 እንዲሁም በግብር ከፋዮች ለቀረበው ቅሬታ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ባለመሰጠቱ ያልተሰበሰበ ግብር በ3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 58,036,507.02፤ በ2 መ/ቤቶች ደግሞ ከሰጡት አገልግሎትና የዱቤ ሽያጭ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ሂሳብ ብር 426,577,775.92 በድምሩ ብር 689,728,015.18 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

26. ውዝፍ ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ብር 391,213,272.36 (ከተወረሱ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሽያጭ እስከ 7 ዓመታት የቆየ)፣ ኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት ብር 109,325,214.55፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር

35,364,503.56፣ የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ብር 35,134,372.40፣ መቀሌ ቅ/ፅ/ቤት ብር 34,073,495.91፣ ጅማ ቅ/ፅ/ቤት ብር 23,745,392.55፣ አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 16,394,111.76 እና የምዕራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 15,338,315.92 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ የዱቤ ሽያጭን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውዝፍ የቤት ኪራይን በወቅቱ አለመሰበሰብ፣ ውሳኔ ወጥቶላቸው በቅሬታ ሰሚ እጅ ያሉ እንዲሁም ቅሬታ ያልቀረበበት እና ቅሬታ ሰሚ ውሳኔ ሰጥቶባቸው ለበርካታ ዓመታት ያልተሰበሰበ ውዝፍ ግብር እና በመሳሰሉት የገቢ አሰባሰብ ችግሮች የተነሳ ሳይሰበሰብ የቆየ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡

27. በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው፣ ማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት አገልግሎቶች ለማስፋፋትና መሠረተ ልማት ለመዘርጋት፣ እንዲሁም ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፤ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ</u>

28. በበጀት ዓመቱ ገቢን እንዲሰበስቡ በተፈቀደላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች ብር 76,700,098.25 እና በሌሎች አምስት መ/ቤቶች ገቢው ባለመመዝገቡ በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ የውስጥ ገቢ ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡

29. የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱት መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ ይህ አሰራር በገቢ ሂሳብ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ለምዝበራ በር የሚከፍት ከመሆኑም በላይ፣ መ/ቤቶቹ በራሳቸው የሚያዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎችና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡

30. በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ማንኛውንም የመንግስት ገቢ ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንዲሰበስቡና በሂሳብ መግለጫዎቻቸው በመካተት ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ በዚህ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በማይወስዱ፣ የመንግሥትን ገቢ ሰብስበው መዝገብ የማይይዙና የሚደብቁ መ/ቤቶች ላይ መንግሥት ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

<u>ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

31. የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች እና በ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 7,875,053.47 እና በሌሎች 6 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ ገቢው ባለመመዝገቡ የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ካላስቻሉ ገዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ አግባብ ባለው አካል የጸደቀ የገቢ ታሪፍ /የማስከፈያ ተመን/ ባለመኖሩ፣ የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፣ የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

32. ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች ዝርዝር በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች</u>

33. በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

- በበጀት ዓመቱ ከተስተናገዱትና ለኦዲት እንዲቀርቡ ከተጠየቁት ዲክላራሲዮኖች መካከል ከሶስት ቅ/ጽ/ቤቶች/ በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት በኩል 118፣ በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት 5፣ የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት 366 ዲክላራሲዮኖች በድምሩ ብዛታቸው 489 የሆኑት ዲክላሳዮኖች ለኦዲት

ሊቀርቡ ባለመቻላቸው በእነዚህ ዲክላራሲዮኖች የተሰበሰበውን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፤

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባወጣው የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል ግብር መመሪያ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 3.4 ላይ ከ2006 የበጀት ዓመት ጀምሮ ኩባንያዎች ትርፍ ለባለ አክሲዮኖች ያከፋፈሉ ወይም የኩባንያውን የካፒታል መዋጮ ለማሳደግ ያዋሉ መሆኑን የሚገልፅ ሪፖርት እና ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማቅረብ እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት 51 እና በጅማ ቅ/ፅ/ቤት 5 ድርጅቶች የአክሲዮን ትርፍ ለባለ አክሲዮኖች ማከፋፈላቸውን ወይም የድርጅቱን ካፒታል ለማሳደግ ያዋሉ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አለመቅረቡ፡

➢ በገቢ ግብር አዋጅ 286/2002 ክፍል 1 አንቀጽ 38 በተቀመጠው የግብር አስገቢው ስልጣንና ተግባር መሰረት በተከታታይ ኪሳራ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች ላይ ስለሚደረገው ክትትል ለማጣራት ሲሞከር በምዕራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኦዲት በናሙና ከታዩት ግብር ከፋዮች መካከል ሁለት (2) ግብር ከፋዮች ከአራት እስከ ስምንት ዓመት በተከታታይ ኪሳራ ያሳዩ መሆኑንና ምንም ዓይነት ማጣራት አለመደረጉ ታውቋል፡፡፣

<u>በሌሎች መ/ቤቶች የሚታዩ የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች</u>

34. ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣

➢ በ5 መ/ቤቶች ለደመወዝና ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች ክፍያ ብር 7,217,491.03 የተፈጸመ ቢሆንም፣ ከክፍያው ላይ የገቢ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፣

➢ የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ በ6 መ/ቤቶች ብር 4,547,250.31 መገኘቱ፣

- የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ብር 2,597,743.62 በብድር ከተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ ያልተደረገ /ያልተሰበሰበ/ ሂሳብ መኖሩ፣
- የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት የገቢ ሂሳብ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 111,476.47 መገኘቱ፣

በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

35. በመሆኑም የመንግስት ገቢ የገቢ አዋጆች፣ ደንብና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ እንዲከናወንና ለታዩትም ድክመቶች አስፈላጊውን ማስተካከያዎች በማድረግ ገቢው እንዲሰበሰብ እናሳስበናል፡፡

የወጪ ሂሣብ

36. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በአግባቡ ወጪ ማድረጋቸውና መጠቀማቸውን፣ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡንና ሂሣቡም በትክክል መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሣብ

37. በወጪ ለተመዘገቡ ሂሣቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ24 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 221,879,238.59 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

38. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች ትምህርት ሚኒስቴር ብር 95,526,864.83፣ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 26,417,436.86፣ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ብር 10,000,000.00፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 8,601,445.18፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,100,434.00፣ ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,646,850.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

39. ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፡ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፣ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣ የዱቤ

ሽያጭ እንጂ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፣ የቀረቡት ተራ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ ስለመዋሉ ወይም ለተቀባዩ ስለመድረሱ የሚገልጽ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጉላ ያሉት ናቸው፡፡

40. ማንኛውም ሂሣብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያ መሠረት ማስረጃዎች መሟላታቸው እንዲረጋገጥ፣ ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉና ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

41. ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈጸሙ ሲጣራ በ56 መ/ቤቶችና 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 61,397,293.70 ከደንብና መመሪያ ውጭ አላአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

42. ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 15,062,986.00፣ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,980,512.79፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 6,837,046.79፣ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,329,915.35፣ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ብር 2,261,095.55፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,798,720.53 እና የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,087,760.45 ሲሆኑ፤ ከምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈጸም፣ ለሠራተኞች አበል፣ ደመወዝና ማበረታቻ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ በመፈጸም፤ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈል፣ የምግብና መኝታ አገልግሎት ተከፍሎ እያለ በተጨማሪ የውሎ አበል በመክፈል፣ የፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የሃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ክፍያ መፈጸም እና መ/ቤቱን ለለቀቁና ለትምህርት ውጪ ሄደው በዚያው ለቀሩ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

43. በመሆኑም ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ የተከፈለው ሂሣብ ተመላሽ እንዲሆንና ለወደፊቱም ደንብና መመሪያዎች ተከብረው መሰራት እንዳለበት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች አሳስበናል፡፡

የተሰበሰበው ግብርና ታክስ በወቅቱ ባለመከፈል ከመ/ቤቶች የተከፈለ ቅጣት

44. የመንግሥት መ/ቤቶች የከፈሉት ወጪ ትክክለኛነት ሲጣራ በ4 መ/ቤቶች የሰበሰቡትን ገቢ በወቅቱ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ባለማድረጋቸው በድምሩ ብር 1,145,629.42 ቅጣት ከፍለው ተገኝቷል፡፡ የመንግሥት መ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ገቢ በህግ በተቀመጠው አግባብ በወቅቱ ለሚመለከታቸው የመንግስት አካል ገቢ ሊያደርጉ ሲገባ ይህንን የተጣለባቸውን ህጋዊ ሀላፊነት በአግባብ ባለመወጣታቸው መንግሥት ሊቀጣ ስለማይገባ ሀላፊነታቸውን ያልተወጡ ሠራተኞችና ሀላፊዎች ተጣርቶ መ/ቤቶቹ የተቀጡት ቅጣት ከሠራተኞቹና ሀላፊዎቹ ተሰብስቦ ለመንግሥት ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርጉና ሥራን በአግባቡ ያልተወጣ ሠራተኛና ሀላፊ ተጠያቂ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በብልጫ የተከፈለ ወጪ

45. በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፣ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ9 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 15,039,356.66 እና በ9 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 1,731,694.61 በጠቅላላው ብር 16,771,051.27 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በ4 መ/ቤቶች ብር 2,133,311.01 በድጋሚ የተመዘገበ ወጪ ተገኝቷል፡፡

46. በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ያለበቂ ምክንያት ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤ በድጋሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገባው ውል ውጭ በመክፈል፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ

በመክፈል እንዲሁም ለትርፍ ሰዓት፤ለተለያየ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተፈቀደው በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

47. ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡ በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁን፤ ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ወጪ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>የግዢ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዢዎች</u>

48. የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ77 መ/ቤቶችና 5 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 546,059,783.00 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

49. ከግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 161,399,723.74፣ አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 81,187,004.35፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 44,669,141.93፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 33,285,467.58፣ የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 25,961,711.36፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 24,639,473.79፣ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 20,278,574.57፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 17,995,122.49 እና ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 17,052,194.00፤ ትራንስፖርት ሚኒስቴር ብር 15,187,734.36 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

50. ከዚሁ በተጨማሪ በ6 መ/ቤቶች ያለውል ስምምነት የብር 21,808,781.25 ክፍያ ፈጽመው ተገኝቷል፡፡

51. ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ ጨረታ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን ግዥ ፕሮፎርማ ሳይሰበስቡና ውድድር ሳይደረግ ግዥ መፈጸሙ እና የተለያዩ ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ ብቻ መፈጸም የሚሉት ይገኙበታል፡፡

52. የግዥ መመሪያንና የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንቦችን ሳይከተሉ ግዥ መፈጸም ለምዝበራና ለጥራት መጓደልና ለግብር ስወራ ጭምር የሚያጋልጥ በመሆኑ፣ የመንግሥት ግዥ ደንብና መመሪያን አክብረው በማይሠሩ መ/ቤቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለትና በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

53. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ13 መ/ቤቶች በብር 9,694,291.99 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበለት እንዲሁም 7 መ/ቤቶች ብር 358,063,033.00 ቀረጥ ተከፍሎላቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን ያለአግባብ በወጪ መዝግበው ተገኝቷል፡፡

54. ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 7,064,490.00፣ የምግብ መጠጥና ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 1,424,000.05 እና የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ብር 181,760.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

55. ቀረጥ ተከፍሎላቸው ንብረቶቹ ገቢ ስለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል የቀድሞው የቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት ብር 321,500,900.33፣ ትምህርት ሚ/ር ብር 17,059,131.50፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 11,989,874.47 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

56. ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብም ሆነ ቀረጥ ተከፍሎላቸው ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ለወጣው ወጪ አገልግሎት ስለማግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዛው ንብረት ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

57. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ

የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

58. በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ በደንብና በመመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 7,064,490.00 እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ብር 6,629,165.34 ለኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያና ለሌሎች ወጪዎች በድምሩ ብር 13,693,655.34 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዘግቦ ተገኝቷል፡፡

59. ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለባቸው፡፡ ተገቢውና ጠንካራ ክትትል ካልተደረገ በቀር በወጪነት የሚመዘገብ ቅድሚያ ክፍያ አገልግሎት ሳይገኝ ባክኖ የመቅረት ዕድሉ እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡

60. በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብለት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ

61. በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ25 መ/ቤቶች ብር 110,624,045.82 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 26,817,229.49፣ የሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ብር 40,150,000.00 እና የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የሲቪል

ሰራተኞች ደመወዝና አበል የተከፈለ ብር 28,653,118.45፣ እና የዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 3,709,426.53 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

62. ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት የሚዳርግ በመሆኑ ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ፤ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ በቂ ማስረጃ እንዲቀርብለት፣ አለበለዚያ ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የማማከር ፈቃድ ሣይኖር ያለአግባብ ተረጋግጦ የተፈጸመ ክፍያ

63. ማንኛውም ግንባታ ሲከናወን ሥራው በትክክል ስለመሠራቱ ብቃቱ ተረጋግጦ የማማከር አገልገሎት እንዲሰጥ በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ፈቃድ በተሰጠው አማካሪ ድርጅት ሲረጋገጥ ብቻ ክፍያዎች ሊፈጸሙ ይገባል፡፡ ሆኖም በ4 መ/ቤቶች የፕሮጀክቶችን ሥራ እንዲከታተሉ የተቋቋሙ፤ ነገር ግን የማማከር ፈቃድ በሌላቸው የግንባታ ጽ/ቤቶች በኮንትራክተሮች የተሠራው ሥራ ትክክለኛነት እየተረጋገጠ በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 717,312,735.03፤ ዲላ ዩኒቨርሲቲ 74,495,345.59፤ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ 35,419,596.22 እና አክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 7,428,032.90 በድምሩ ብር 834,655,709.74 ገንዘቡ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

64. ስራው በዲዛይኑና በተገቢው ጥራት ስለመሠራቱ የሚሰጠው ማረጋገጫ በህግ አግባብ ዕውቅና በተሰጠው አካል ካልተፈጸመ የተከናወነውን ግንባታ አስመልክቶ ችግር ቢፈጠር ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ስለማያስችል መ/ቤቶቹ እየተከተሉት ያለው አሠራር በፍጥነት እንዲቋረጥና ለግንባታዎች ተገቢው ዕውቅና ያለው አማካሪ ድርጅት እንዲቀጠር አሳስበናል፡፡

በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

65. ከውስጥ ገቢ እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸው ያወጡትን ወጪና ሌሎች መ/ቤቶችም የተከፈለውን ገንዘብ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት አካተው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚያቀርቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ4 መ/ቤቶች ብር 16,920,367.57 እና በሌሎች 4 መ/ቤቶች ሂሳቡ ባለመመዝገቡ መጠኑ በገንዘብ ያልተገለጸ ከውስጥ ገቢ

የተከፈለና የሌሎች ወጪ ሂሳብ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ተካቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

66. ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ የገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ የመ/ቤቶቹን ትክክለኛውን የፋይናንስ አፈጻጸምና ገፅታ እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

67. ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችንም በተደጋጋሚ እንደተገለፀው በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት ብናሳስብም በአንዳንድ መ/ቤቶች ሊታረም ባለመቻሉ በም/ቤቱ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የተከፋይ ሂሣብ

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

68. በገ/ኢ/ት/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ55 መ/ቤቶችና በስምንት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,039,053,017.42 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

69. በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች፣ በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 573,375,335.26፣ ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 140,672,253.79፣ ዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 66,326,640.75፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 53,599,028.31 የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ማህበራት ኤጀንሲ ብር 29,170,083.93፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጅማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 24,601,870.61፣ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ብር 22,909,946.60፣ በአድግራት ዩኒቨርሲቲ ብር 18,958,704.29 እና የሐዋሳ ዩኒቨርስቲ ብር 17,122,223.91 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

70. በመሆኑም የተመለከተው ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ በፋይናንስ ሕጉ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ሊከፈል ይገባል፡፡

በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ድክመቶች

71. በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶችና በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 78,579,156.42 መኖሩ፣
- በተከፋይ ያልተመዘገበ የመያዣ ሂሳብ በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,995,104.05 መገኘቱ፣
- መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ በ7 መ/ቤቶች ብር 213,309,829.63 መገኘቱ፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው በ2 መ/ቤቶች ብር 6,696,197.00 መገኘቱ እና ሌሎች ሌጃር አዘጋጃጀትና አያያዝ ችግሮች እንደሚታይባቸው ተረጋግጧል፡፡

72. በዚህ ሁኔታ የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ገፅታ ስለማያሳይ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ በፍጥነት ሊወሰዱ ይገባል፡፡

የበጀት አጠቃቀም

ከበጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ

73. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት በ41 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸውና ከተደለደለው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱና በጀት ሳያዛውሩ ከመደበኛ በጀት ብር 621,319,554.74 እና ከካፒታል በጀት ብር 124,831,405.18 በድምሩ ብር 746,150,959.92 ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

74. ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱና ሳያዛውሩ ሥራ ላይ ካዋሉት መ/ቤቶች መካከል የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 186,511,080.05፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር

123,560,176.47፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 54,131,615.00፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 43,010,493.00፣ ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 39,080,757.06፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 35,861,587.36፣ አሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 35,343,027.00፣ እና ዲላ ዩንቨርሲቲ ብር 35,110,366.58 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

75. ከዚህ በተጨማሪም የመንግሥት ፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ ለስራው ምንም በጀት ሳይያዝ ብር 454,342.50 ወጪ አድርጎ ተገኝቷል፡፡

76. በጀት ሳይፈቀድ ወይም ዝውውር ሳይደረግ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ በመሆኑ መ/ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ እንደዚሁም በበጀት አዋጁ መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት የተቀመጠውን አሠራር በመከተል በተገቢው መንገድ የበጀት ዝውውር በማድረግ አስፈቅደው ሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡ ነገር ግን ይህ ጉዳይ እየተሻሻለ ባለመሆኑ ም/ቤቱና የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተገቢውን አፋጣኝ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

የንብረት አስተዳደር

77. መንግሥት ለቋሚና አለቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው የዕቃና ንብረት አስተዳደር በዚህ ዓመትም አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ፣

ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	29 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በማመሳከር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	24 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	15 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ	27 መ/ቤቶች
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	11 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	24 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች	55 መ/ቤቶች

በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	21 መ/ቤቶች
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	13 መ/ቤቶች
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸው	8 ቅ/ጽ/ቤቶች
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ ያላደረጉ	8 መ/ቤቶች
የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማያረጋግጡ	4 መ/ቤቶች
በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሳይደረጉ ንብረት ክፍል የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው መ/ቤቶች	6 መ/ቤቶች
ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	12 መ/ቤቶች

መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

78. በመሆኑም የየመሥሪያ ቤቶቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲመራ፣ በታዩት ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ፣ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ

79. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ32 መ/ቤቶች	313 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ21 መ/ቤቶች	218 ተሽከርካሪዎች
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	በ6 መ/ቤቶች	15 ተሽከርካሪዎች
የባለቤትነት መታወቂያ	በ4 መ/ቤቶች	38 ተሽከርካሪዎች

ደብተራቸው በሌሎች መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ		
ሊብሬ ብቻ ሲገኝ ተሽከርካሪዎቹ በአካል ያልተገኙ	በ1 መ/ቤት	10 ተሽከርካሪዎች
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት	በ2 መ/ቤቶች	3 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ታውቋል፡፡

80. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው፣ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው፤ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ፣ ሊብሬ ያልቀረበላቸው አስፈላጊው ማስረጃ ተሟልቶ እንዲወጣላቸውና በአካል ያልተገኙት ተሽከርካሪዎችም ያሉበት ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>መሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተ</u>

81. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS III) ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተልኮ ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍነው የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

82. በዚህም መሠረት ከሁሉም ክልሎች በናሙና በተመረጡ በ300 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ የክልል ሴክተር ቢሮዎች ተከታታይ ኦዲት (Continuous Audit) እና አንድ ፕሮግራም አቀፍ የሆነ የማጠቃለያ (final audit) ኦዲት ለማካሄድ ታቅዶ በ294 (98%) ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ

በሆኑ የሴክተር ቢሮዎች እንደዚሁም ፕሮግራም አቀፍ የሆነውን የማጠቃለያ (final audit) ኦዲት በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ደረጃ ለመፈጸም ተችሏል፡፡

የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ

83. በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የተዘጋጀው የ2007 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላከ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት የታዩት ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

84. መንግስት ከውጭ ሀገር ተበድሮ በመልሶ ማበደር ስምምነት መሰረት ለልማት ድርጅቶች ያበደረውን ገንዘብ ተበዳሪዎች በገቡት ውል መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ተመላሽ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ እስከ ሰኔ 30/2007 ዓ.ም ድረስ ከተለያዩ አራት ድርጅቶች ላይ ወለድን ጨምሮ በድምሩ ብር 472,672,766.89 ለመሰብሰብ ታቅዶ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

85. የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2.ለ መሠረት የእያንዳንዱ የሂሳብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን /ዴቤት ወይም ክሬዲት/ ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡በመሆኑም ከ2006 በጀት ዓመት የዞረው መነሻ ሂሳብ ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ተጠብቆ ለ2007 በጀት ዓመት የሂሳብ መነሻና መክፈቻ ሆኖ መተላለፉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5052 የፍርድ ቤት መያዣዎች እና በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5054 ሌሎች የመያዣ ሂሳቦች ከ2006 በጀት ዓመት የተላለፈ ብር 9,425,908.87 ለ2007 የመነሻና የመክፈቻ ሂሳብ ክሬዲት ሆኖ መተላለፍ ሲገባው በዴቢት ተመዝግቦ የተላለፈ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

የክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች በተመለከተ

86. የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናትን ተከትሎ መ/ቤታችን የፋይናንስና የሕጋዊነት (regularity) ኦዲቱን ሽፋንና ጥራት በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በሂደት ትኩረቱን በክዋኔ ኦዲት ላይ የማድረግ አቅጣጫን ለመከተል

በተወሰነው መሰረት በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጄክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መምታታቸውን ለማረጋገጥ የክዋኔ ኦዲት ተከናውኗል፡፡

87. በዚሁ መሠረት ከየካቲት 2007 በፊት ተጀምረው ዝርዝር የኦዲት ስራቸው ወደዚህኛው የኦዲት ዓመት የዞረ 1 ክዋኔ ኦዲትና ከየካቲት 2007 በኋላ ተጀምረው እስከ ጥር 30 የሚጠናቀቁ 19 እንዲሁም ተጀምሮ ወደሚቀጥለው ዓመት የሚዞር 1 ክዋኔ ኦዲት በድምሩ 20 የክዋኔ ኦዲቶችን ለማከናወን በእቅድ የተያዘ መሆኑ ይታወቃል፡፡

88. የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈጻፀም ሲታይ ካለፈው ዓመት የዞረውን 1 ኦዲት ጨምሮ በዚህ የእቅድ ዘመን ወጪ መደረግ ከሚገባቸው 19 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ውስጥ የ17 ኦዲቶች ሥራ ተጠናቅቆ ሪፖርታቸው የተላከ ሲሆን፣ አንድ ኦዲት ሥራው ተጠናቅቆ የመወጫ ስብስባ ባለመደረጉ ወጪ ያልሆነ፤ አንድ በዓመቱ ውስጥ ሊጀመር የነበረው ኦዲት ደግሞ ተቋርጦ በምትኩ 4 የክትትል ኦዲቶች ተከናውኖ ሪፖርቶቹ ቀርቧል፡፡ አንድ ኦዲት ደግሞ በዕቅዱ መሠረት ተጀምሮ ሥራው ወደ ተከታዩ ዓመት ተሻግሯል፡፡

89. ይህም ከእቅድ አንጻር ሲታይ ሥራው ተጠናቅቆ የመውጫ ስብሰባ ባለመደረጉ ወጪ ካልሆነው በስተቀር የክዋኔ ኦዲቶቹም በታቀደው መሰረት ተከናውኗል፡፡ የኦዲት ሪፖርታቸው ወጪ የሆኑት 17 የክዋኔ ኦዲቶችና የ4ቱ የክትትል ኦዲት ሪፖርቶች ለም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን፣ ዋና ዋና ግኝቶች በአጭሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

<u>በከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ጥራት ላይ የሚያደርገውን የክትትልና የግምገማ በተመለከተ</u>

90. የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀፅ 89 ተራ ቁጥር 5 መሰረት ኤጀንሲው በማንኛውም ተቋም የሚሰጡ ከፍተኛ ትምህርት እና ስልጠና ከአገሪቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መገናዘባቸውን ኤጀንሲው ማረጋገጥ ያለበት ቢሆንም

በኦዲት ወቅት በደብረማርቆስ፣ በባህርዳር እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲዎች በተቋማቱ የምሩቃኖቻቸውን መዳረሻና የቀጣሪዎቻቸውን እርካታ በማጥናት ከጥናቱ ያገኙትን ግብረ-መልስ እንደግብዓት በመጠቀም ሥርዓተ ትምህርታቸውን የሚያጎለብቱበትንና የሚያሻሽሉበትን እንዲሁም ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት የሚፈለጉ ብቁ ዜጎችን ማፍራቱን የሚከታተሉበት የአሰራር ስርዓቱ የሌላቸው መሆኑን፤

91. ኤጀንሲው በሁሉም የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ለትምህርት አሰጣጥ የሚያገለግሉ ቤተሙከራዎች እና ሌሎች መገልገያዎች በተቀመጠው መስፈርት ተግባራዊ መደረጋቸውን መከታተልና እርምጃ ሊወስድ የሚገባ ቢሆንም ከተከለሱ የኤጀንሲው የጥራት ኦዲት ሪፖርቶች እንዲሁም በመስክ ኦዲት ወቅት የኦዲት ቡድኑ ተዘዋውሮ ባያቸው ተቋማት የተገኙት ግኝቶች በተለይ በምህንድስና፣ በሳይንስና በሕክምና ዘርፎች ያሉ ቤተሙከራዎች በአብዛኛው ለዘርፉ አስፈላጊ በሆኑ መሳያሪዎችና ግብዓቶች ያልተደራጁ መሆኑ፤

92. የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀፅ 40 ተራ ቁጥር 3 የተቋሞች ሕንፃ ዲዛይን የግቢዎቻቸው ተፈጥሯዊ አቀማመጥ ኮምፒውተሮቻቸውና ሌሎች የመገልገያ አውታሮቻቸው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ፍላጎት ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን እንዳለበት ቢደነግግም አዳዲስ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሲሰሩም እና የነባሮቹ የማስፋፊያ ግንባታዎች በአንዳንድ ተቋማት ሲከናወኑ የደረጃ መውጫ መንገድ ከመሰራቱ በስተቀር በሌሎች አገልግሎቶች ላይ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑ በመስክ ኦዲቱ ወቅት በተደረገ ጉብኝት እና መጠይቁ ከቀረበላቸው ኃላፊዎች እንዲሁም በናሙና መጠይቅ የቀረበላቸው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ለመረዳት መቻሉ፤

93. በኦዲት ወቅት በናሙና በታዩ በደብረማርቆስ፣ ባሕርዳር እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎች በአካዳሚክ ውጤታቸው ብቻ የሚመዘኑበት፤ በሌላ በኩል በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የነበረውን አፈጻጸም በተመለከተ አስተማሪዎች ደግሞ በተማሪዎች የሚመዘኑበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ የተደረገ ቢሆንም ተማሪዎች በተሰጠው ምዘና ላይ የሚያቀርቡት

ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት የተሻለ ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም መምህራን በተማሪዎች የሚሰጣቸውን ምዘና ላይ የሚያቀርቡት ቅሬታ ግን የሚስተናገድበት ሥርዓት አለመኖሩ በናሙና ያነጋገርናቸው መምህራን የገለጹ ከመሆኑም በላይ መምህራኑ ተማሪዎች ፍትሃዊ በሆነ መልኩ መምህራኖቹን ይመዝናሉ ብለው እንደማያምኑ ይልቁንም ተማሪዎቹ ምዘናውን የሚያከናውኑት ከመምህራኑ ማስተማር ብቃት ጋር አያይዘው ሳይሆን ከአስመዘገቡት የአካዳሚክ ውጤት ጋር አያይዘው መሆኑን፣ በዚህም ምክንያት አነስተኛ የምዘና ውጤት ላለማግኘት ወይም አላባቃችሁም ተብለው ድጋሚ አስተምረው ላለመፈተን በሚል መንፈስ አስተማሪዎች የፈተና ውጤት እንደሚሰጡ በናሙና መጠይቅ የቀረበላቸው መምህራን የገለጹ መሆኑ፤

በፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የድጋፍ ማዕቀፎች አፈጻጸምን በተመለከተ

94. የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራዞች የሚደረገውን የብድር አቅርቦት ድጋፍ በተመለከተ በአምስት ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ አካቶ ያቀደ ቢሆንም የብድር ስርጭት በዕቅዱ መሠረት ባይከናወንም (በ2004 51%፣ በ2005 75%፣ በ2006 75%፣ በ2007 86%) እየተሸሻለ የመጣ ሲሆን በተጠቃሚዎች ብዛት ግን አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ (በ2004 14%፣ 2005 24%፣ 2006 16% እና 2007 ዓ.ም 31%) መሆኑ፤

95. በኤጀንሲው የአምስት ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር ዋስትና ፈንድ አሰራርና አተገባበር ጋይድ ላይን የብድር አገልግሎት ፈላጊ ኢንተርፕራይዞች ብድር ለማግኘት በመደበኛ ባንኮች የተቀመጡትን የብድር ዋስትና/ማስያዣ (collateral) የማቅረብ አቅም ስለሌላቸው ሥራቸውን ለመጀመር ወይም ለማስፋፋት የሚያስችል ብድር ለማግኘት ስለሚቸገሩ የክልል መንግስታት በክልላቸው በየዓመቱ ሊሰጥ የታቀደውን የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን የብድር ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት በየዓመቱ የሚታደስ የብድር ዋስትና ፈንድ እንደሚያቋቁሙ በዘርፉ ልማት ስትራቴጂ የተመለከተ ቢሆንም በናሙና በታዩት ክልሎችና

ከተማ አሰተዳደር ውስጥ ከአዲስ አበባ ከተማ በስተቀር በሌሎች ክልሎች የብድር ዋስትና ፈንድ አለመቋቋሙ፤

96. በተቀመጠው ጋይድላይን መሠረት የብድር ዋስትና ፈንድ ባለመቋቋሙ የከተማ መስተዳድሮች በራሳቸው ተነሳሽነት ለኢንተርፕራይዞች የብድር ዋስትና ሽፋን በመስጠት ብድሩ ቢመቻችም፤ ኢንተርፕራይዞች የተበደሩት ገንዘብ በማስመለስ ሂደት ላይ መንግስት ዋስ ሆኖልናል በሚል የተሳሰተ አስተሳሰብ ብድር ማስመለስ ረገድ ችግር እያጋጠመ መሆኑን በናሙና የታዩ በሃዋሳና ሻሸመኔ ከተሞች የሚገኙ አነስተኛ ብድር አቅራቢዎች የገለጹ መሆኑ፤

97. በ5 ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የማምረቻ፣ መሸጫና ገበያ ክላስተር ልማት አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 002/2003 ዓ.ም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በምርትና አገልግሎት ስራዎች ለመሰማራት እንዲችሉ ምቹ በሆኑ ቦታዎች መሰረተ ልማት የተሟላላቸው፤ ህንጻዎችና ሼዶች በመገንባት በመጠነኛ ኪራይ ለማቅረብ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመለከትናቸው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሐዋሳ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በሻሸመኔ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በታዩ ማዕከላት ግንባታቸው ተጠናቀው ሁለት ዓመት ቢያስቆጥርም ልዩ ልዩ መሰረተ ልማቶች ባለመሟላቱ ለኢንተርፕራይዞቹ ያልተላለፉ መኖራቸው፣ ለኢንተርፕራይዞቹ ተላልፈው ሥራ የተጀመረባቸው አንዳንድ ማዕከላትም ቢሆኑ መሰረተ ልማቶቹ ሳይሟላላቸው የተላለፉ በመሆኑ ተጠቃሚዎች ላይ ችግር ማስከተላቸው እንደዚሁም የሼዶች ግንባታ ዕቅድ አፈጻጸምም ሲታይ በ2004 50%፣ 2005 43%፣ 2006 88% እና በ2007 69%፣ የህንፃዎች ግንባታ ደግሞ በ2004 74%፣ 2005 41%፣ 2006 41% እና በ2007 37% ላይ መገኘቱ፤

የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የሚያስተዳድራቸው ቤቶች አስተዳደር እና የስራ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ መከናወኑን በተመለከተ

98. ኤጀንሲው ቤት የማግኘት መስፈርት ላሟሉ ደንበኞች በኪራይም ሆነ በነፃ የሚያከራያቸው የመኖሪያም ሆነ የድርጅት ቤቶችን ቤት በሚያከራይበት ጊዜ የቤት ኪራይ ውል ሊዋዋልና ውሉም በየአመቱ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ

ዉሉን ሊያድስ በማያድሱት ላይም በውሉ መሰረት ተገቢውን እርምጃ ሊወሰድ የሚገባ ቢሆንም፤ በየዓመቱ ውል የማያድሱ ደንበኞች ያሉ መሆኑ፣ ኤጀንሲውም በየዓመቱ ውላቸውን በማያድሱት ደንበኞች ላይም ለአንዳንዶች ደብዳቤ እንዲያድሱ ከመፃፍ ውጪ በዓመቱ ወይም በሁለት ዓመት ሊያድሱ ሲመጡ የሚወሰድ እርምጃ አለመኖሩ፤ እንደዚሁም ከኪራይ ነፃ ቤት ከሚሰጣቸው ደንበኞች ጋር ምንም አይነት ውል የማይገባ መሆኑ፤

99. የውል ግዴታቸውን ባለማክበርም ይሁን በሌላ በተለያየ ምክንያት ኤጀንሲው የሚያስተዳድረውን ቤት ከተከራዩት ደንበኞቹ ያልተሰበሰበና መፍትሄ ያላገኘ ብር 98,943,642.56 ያለ መሆኑ፤

100. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም በተለያየ ምክንያት የተወረሱ ንብረቶችን የያዙ 19 ትላልቅ መጋዘኖች ተዘግተው እንደዚሁም ከጥገናና ዕድሳት የተመለሱ ነገር ግን መወገድ ወይም በተለያየ መንገድ ሥራ ላይ መዋል የነበረባቸው ንብረቶች ከመጋዘን ውጭ ተቀምጠው እየተበላሹና ከጥቅም ውጪ እየሆኑ የሚገኙ መሆኑ፤

በመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የመድኃኒት እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ አፈጻጸም በተመለከተ

101. ኤጀንሲው ዓመታዊ የመድኃኒት አቅርቦት ጥያቄ ከጤና ቢሮዎችና ከጤና ተቋማት በየዓመቱ የሚሰበስብ ቢሆንም ፍላጎቶቹ በበጀት የተደገፉ መሆናቸውን ግን እንደማያረጋግጥ፣ የተሰበሰበውን ዓመታዊ የመድኃኒት እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች አቅርቦት ጥያቄ በመጠን፣ በጊዜና እና በገንዘብ በመተንተን በቀረበው ፍላጎት መሰረት የመድኃኒት ግዢ እቅድ የሚያዘጋጅና ዓመታዊ የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ በጀቱን ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ስለማስፀደቁና ስለማስፈቀዱ እንደዚሁም በግዥ አዋጁ መሰረት ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዕቅዱን ስለመላኩ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መረጃ ሊያቀርብ አለመቻሉ፤

102. ኤጀንሲው የሚያከናውናቸውን የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ግዥ በጊዜ፣ በአይነት፣ በመጠን፣ በገንዘብ እና ለማን እና ከየትኛው በጀት እንደተገዛ በሚያሳይ መልክ ተዘርዝሮ ሊመዘገብ የሚገባ ቢሆንም ከ2003

ጀምሮ የተገዙ መድኃኒቶች መቼ፣ ለማን፣ እና ከየትኛው በጀት እንደተገዙ የሚያሳይ ግልጽ ምዝገባና መረጃ የሌለ መሆኑ፤

103. የጤና ተቋማት በየጊዜው እንዲገዛላቸው በዓመቱ መጀመሪያ ላይ የሚጠየቁ አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች በወቅቱና በጠየቁት መጠን እንዲደርሳቸው ሊደረግ ሲገባ በኦዲቱ ወቅት በናሙና መጠይቅ የቀረበላቸው አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ሆስፒታሎች ፍላጎታቸውን ለኤጀንሲ ቢያሳውቁም ኤጀንሲው ከቀረቡት የፍላጎት ማሳወቂያ ዝርዝር ውስጥ መኖሩን በማረጋገጥ ሊሰጣቸው የሚችለው 30 ከመቶ ብቻ ያህሉን መሆኑን፤ እንደዚሁም ለሆስፒታሎች አገልግሎት የመጡ መሳሪያዎች የመለዋወጫና የኬሚካል እጥረት ችግር ያለባቸው በመሆኑ መሣሪያዎቹ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑና የኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም ቢሆን መድኃኒቶች በበቂ ሁኔታ የማይሰጣቸውና አልፎ አልፎም የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የተቃረበ መድኃኒቶች እንደሚሰጣቸው መግለጻቸው፤

104. በኤጀንሲው ተገዝተው የሚመጡ መድኃኒቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ሳያልፍ ለተገዙላቸው የጤና ተቋማት በማሰራጨት ሥራ ላይ ሊውሉ ሲገባ ይህ ባለመሆኑ ከ2005 እስከ 2007 ባለው ጊዜ ብቻ በከፍተኛ ገንዘብ የተገዙ በዋናው መስሪያ ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መጋዘኖች በድምሩ ብር 569,833,919.27 (አምስት መቶ ስድሳ ዘጠኝ ሚሊየን ስምንት መቶ ሰላሳ ሦስት ሺ ዘጠኝ መቶ አሥራ ዘጠኝ ብር ከ 27/100) የሚያወጣ የአገልግሎት (የመጠቀሚያ) ጊዜያቸው ያለፈባቸው (EXPIRED) መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ የአገልግሎት (የመጠቀሚያ) ጊዜው ያለፈበት (EXPIRED) መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች ኬሚካሎችም ጭምር አገልግሎት ከሚሰጡ መድኃኒቶች ጋር አብሮ በመጋዘን ውስጥ እንዲቀመጡ መደረጉ፤

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የእግር ኳስ ስፖርትን ለመምራት እና ለማስፋፋት እያከናወነ ያለውን የአሠራር ሥርዓት በተመለከተ

105. ፌዴሬሽኑ ከ2001-05 ባለው ስትራቴጂክ እቅዱ ላይ የሀገር ውስጥ ውድድሮች በዞን፣ በወረዳ፣ በቀበሌና በትምህርት ቤቶች፣ የክለብ ታዳጊዎች ሻምፒዮናና

አዳዲስ የውድድር ዓይነት የመፍጠር ስራዎችን፣ የኢንተርናሽናል ውድድሮች በምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ፣ ኢንተርናሽናል የወዳጅነት ጨዋታዎች ማድረግን እና የስፖርት ህክምና ስልጠና መስጠትን ቢያቅድም እስከ 2005 ዓ.ም ዓመታዊ እቅድ ውስጥ አለማካተቱ፣ የየዓመት የእቅድ አፈፃፀሙን በወር፣ በየሩብ ዓመትና በአመቱ መጨረሻ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እየቀረበ የማይገመገም መሆኑ፤

106. ፌዴሬሽኑ በሁሉም ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች፣ ክለቦችና ፕሮጀክቶች እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ ድጋፍና ክትትል ያላደረገ መሆኑ፣ በ2007 ዓ.ም 11 የክልል ፌዴሬሽኖችን አደረጃጀት በማሻሻል ለእግር ኳሱ ዕድገት እንዲያበረክቱ የማስፈጸም አቅማቸውን ለመገንባት የታቀደ ቢሆንም ያልተከናወነ መሆኑ፣ በየደረጃው የሚገኙ የፕሪሚየርና የብሔራዊ ሊግ ክለቦች አደረጃጀት እንዲሻሻልና የማስፈጸም አቅማቸውም እንዲገነባ ማድረግን እና የክለብ ፈቃድ አሰጣጥ (licensing) ሥርዓትን እንደሚዘረጋ ቢታቀድም ያልተከናወነ መሆኑ፣ የክልል እግር ኳስ ፌዴሬሽኖችና ክለቦች ወጥ የሆነ መዋቅራዊ አደረጃጀት እንደሌላቸው እና በቀድሞ ስፖርት ኮሚሽን ሐምሌ 2004 ዓ.ም የስፖርት ክለቦች ያለባቸውን የአደረጃጀት ችግር ለመፍታት የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት ማንዋል ያስጠና ቢሆንም ፌዴሬሽኑ በክለቦች ላይ ተግባራዊ እንዲሆን አለማድረጉን፤

107. ፌዴሬሽኑ በመተዳደሪያ ደንብ ላይ የተቀመጡ የአባላት ግዴታዎች ሁሉ አባላቱ (የክልል ፌዴሬሽኖች፣ ክለቦች ወዘተ) እየተወጡ ስለመሆኑ የሚከታተልበት ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ ለዚህም እንደማሳያ የሚሆነው በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት ክለቦች (ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ የኢትዮጵያ ቡና፣ ቡራዩ ከተማ፣ ሰበታ ከተማ፣ መቀሌ ከተማ እና ወልዋሎ) ከአባልነት ግዴታዎች ውስጥ ዓመታዊ የአባልነት ክፍያ ብቻ የሚፈፅሙ መሆኑን፣ የክልል እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች ግዴታዎቻቸውን ስለመፈፀማቸው ክትትል የማያደረግ መሆኑ፤

የዓሣ ሀብትን ዘላቂነት ለመጠበቅና ለማልማት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

108. በኦዲቱ ወቅት የዓሣ ሀብትን ለማልማትና ለመጠበቅ የሚረዳ የዓሣ ሀብት ልማትና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 315/1995 ዓ.ም እና በ 2001 ዓ.ም ብሄራዊ የዓሣ ሀብት ልማት ስትራቴጂ የተዘጋጁ ቢሆንም እነርሱን ለመተግበር የሚያግዙ መመሪያዎች አለመዘጋጀታቸው፣ የኢትዮጵያ የአሣ ምርት መቆጣጠሪያ ደንብ በ2005 ዓ.ም በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም ደንቡ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ለሚመለከተው አካል ቀርቦ እንዲጸድቅ አለመደረጉ፣

109. የዓሣ ሀብት የሚገኝባቸው የውሃ አካላት፣ በአካባቢያቸው ዙሪያ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በዓሳ ሀብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድሩ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ሲገባ በናሙና በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች በሚገኙ የውሃ አካላት አካባቢዎች ከሚከናወኑ የልማት ሥራዎች የሚወጡ የኬሚካልና ንጥረ ማዕድን እጣቢዎች፣ ፍሳሾች እና የእርሻ ኬሚካሎች የዓሣ ሀብትን እየጎዱ እንደሆነ ከማሳወቅ ውጪ ችግሩን ለማቃለል በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰራ የቁጥጥርና ክትትልና ስራ አለመኖሩ፣ እንዲሁም በሀይቆችና መጋቢ ወንዞች አካባቢ የኢንቨስትመንት ስራዎች ከመከናወናቸው በፊት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሲሰራ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ የሚመለከታቸው የክልል አካላት አስተያየት እንደማይጠየቁ እና ተሰርቶ ሲያልቅም እንዲያውቁት የማይደረግ መሆኑን፣

110. በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅቶ የጸደቀ የዓሣ ማስገሪያ መሳርያዎች ስታንዳርድ ባለመኖሩ ክልሎች የሚጠቀሙት ከክልላቸው ምርምር ማዕከላት ጋር በመሆን ባወጡት የዓሣ ማስገሪያ መሳርያዎች ስታንዳርድ መሆኑን፣ ህገወጥ የዓሣ ማስገሪያ ድግን መረብ (monofilament) በግብጽ አገር ተመርቶ በሱዳን ድንበር (መተማ) በኮንትሮባንድ እንደሚገባ፣ ዓሣ አስጋሪዎችም ይህን መረብ እየገዙ በመጠቀማቸው ዘር ተኪ ጫጩት ዓሣ ጭምር በመያዝ የዓሳ ዝርያዎች

እየተመነመኑ መሆኑን፣ የዓሣ ማስገሪያ መረብ ከውጪ በማስመጣት የሚያቀርብ አካል ባለመኖሩ እና በሀገር ውስጥም የማይመረት ስለሆነ በኮንትሮባንድ የሚገባውን ህገወጥ ሞኖፊላመንት መረብ በአማራ ክልል፣ በኦሮሚያና ደቡብ ክልሎችም ስታንዳርዱን ያልጠበቀ ተጎታች መረብ የሚጠቀሙ መሆኑ፣ የዓሳ ማስገሪያ መሳሪያዎች በክልሎች ባወጡት ስታንዳርድ መሰረት መስራታቸውን አንዳንዴ ቁጥጥር እንደሚደረግ ነገር ግን ወጥ የሆነ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ያለመኖሩን፣

<u>በቱሪዝምና ባህል ሚኒስቴር የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶችን ብቃት ያለው፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆኑ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ</u>

111. የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች የሚሰጡት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል ደረጃ ሊያወጣ እና ባወጣው ደረጃ መሰረትም ስለመተግበሩ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ሲገባ ኦዲት እስከሚጠናቀቅ ድረስ ለአስጎብኚ ድርጅቶች ደረጃ ያልወጣ መሆኑ፣

112. ማንኛውም አስጎብኚ ድርጅት ከቀረጥ ነጻ የተፈቀደለት ንብረት ወይም ተሽከርካሪ ለማስጎብኘት አገልግሎት ሥራ ብቻ ስለመዋሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ሲገባ የማያደርግ መሆኑ፤

113. በአስጎብኚነት የሚሰማሩ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት የተዘጋጀ ቢሆንም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው አስጎብኚ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች እና ያላቸውን የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ግቢ በአካል አስቀርበው እንዲታዩ በማድረግ ብቻ በመሆኑና ድርጅቶቹ ያቀረቧቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች ትክክለኛነት ባሉበት በአካል በመሄድ እንደማይረጋገጥ እንዲሁም የባለሙያዎቹ የሙያ ብቃት በየጊዜው የማይረጋገጥ ከመሆኑም በላይ ከማስጎብኘት አንጻር ቱሪስቶች በከፈሉት መጠን አርኪ አገልግሎት ስለማግኘታቸው፣ በድርጅቶቹ ላይ የሚታየው የእድገት ለውጥ እና ለቱሪዝም ዘርፉ ያበረከቱትን አስተዋፅኦ ለመለካት የማያስችል መሆኑ፤

<u>በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሠራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነትን ለማስጠበቅ የዘረጋውን የአሰራር ስርዓት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ</u>

114. አሰሪዎች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ በተቋማቸው ስለማቋቋማቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ ቢሆንም መዝግቦ ከያዛቸው 40 የልማት ድርጅቶች ውስጥ አስራ አንዱ ድርጅቶች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ ያላቋቋሙ መሆኑ፤

115. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅቶች ለሠራተኞቻቸው የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ልብስና ሌሎች ቁሳቁሶችን ማቅረባቸውንና ስለአጠቃቀሙ ስልጠና የሚሰጡበት አሰራር መኖሩን እና ተግባራዊ ማድረጋቸውን ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ በናሙና ተመርጠው ከታዩት 11 ድርጅቶች ውስጥ 8ቱ የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ልብስና ሌሎች ቁሳቀሶችን የማያቀርቡ መሆናቸው፤

116. አዳዲስ ድርጅቶች ሲሰሩም ሆነ ነባር ድርጅቶች ሲስፋፉና ሲለወጡ ወይም መሳሪያዎች ሲተከሉ በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ ጉዳት የማያደርሱ መሆናቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የሚገባ ቢሆንም በናሙና በታዩት 11 ድርጅቶች በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች በየወቅቱ ክትትልና ቁጥጥር እንደማይደረግ የታወቀ መሆኑን፤

<u>በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የአምስቱ ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አፈፃፀም በተመለከተ</u>

117. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጭ በሚገኝ እርዳታና ብድር የሚከናወኑ የአምስቱ ከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የብድር እና ዕርዳታ ስምምነት እ.ኤ.አ በ2007 ተጀምሮ በ2012 ለማጠናቀቅ ከአለም አቀፍ የልማት ማህበር (IDA) ጋር የብድር እና የእርዳታ ስምምነት የተፈረመ እና የስምምነት ጊዜው ሲልያቅ እ.ኤ.አ. ከ2013-2015 ለማራዘም ተጨማሪ የብድር እና የእርዳታ ስምምነት የተፈረመ ሲሆን በሁለቱም ስምምነት የተያዙት ስራዎች በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ በመሆኑ አሁንም ለተጨማሪ ጊዜ

እስከ ታህሳስ 2016 ድረስ ለአንድ አመት እንዲራዘም የተደረገ ቢሆንም በናሙና የታዩት ከተሞች ውሃ ፕሮጅክት ጽ/ቤቶች ያሉት ቀሪ ሥራዎች በተጫማሪውም ጊዜ ውስጥ ሊጠናቀቁ እንደማይችሉ የገለጹ መሆኑ፡

118. ለፕሮጀክቶቹ ለመሳሪያዎች እና እቃ፣ ለሥራዎች እና ከማማከር አገልግሎት ውጪ ለሆኑ አገልግሎቶች (non consulting services) ግዥ የቀጥታ የኮንትራት ውል አፈጻጸም (Direct contracting) ከአለም ባንክ የNo-objection (የማረጋገጫ) ምላሽ በወቅቱ እንዲሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ ሲገባ በወቅቱ ባለመፈጸሙ በሐዋሳ የአንደኛው ፌዝ የአምቦ ወሃ ምንጭ የዲሲ አይ እና የፒቪሲ ቧንቧዎች ግዥ ለመፈጸም አቅራቢው ጨረታውን ያሸነፈው በብር ምንዛሬ በመሆኑ እና L/C የሚከፈተው በዶላር በመሆኑ ይህን ለማስታረቅ በመዘግየቱ ብቻ 1 ዓመት ከስድስት ወር መፍጀቱ፣ እንዲሁም የድሬዳዋ ከተማ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት በ2006 ዓ.ም የወጣው የቧንባ ግዥ ጨረታን በተመለከተ የሎት-1 ድሲ አይ ፓይፕስ እና ፊቲንግ እና የሎት-2 ዩፕቪሲ ፓይፕስ እና ፊቲንግ አቅርቦት የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣ ከ18 ወራት መዘግየት በኋላ ኮንትራት መፈረሙ፣ የሎት 2 ዩፒቪሲ ፓይፕስ እና ፊቲንግ አቅርቦት ኮንትራት ከተፈረመ ከሰባት ወር በኋላ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተ መሆኑ፣

119. በከተሞች የሚገነቡ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች የመሳሪያ እና የተለያዩ ዕቃዎች (የፓይፕ፣ የኤሌክትሮሚካኒካል…) ግዥ ሲፈጸም በውሉ መሠረት መከናወኑ ሲጣራ በሐዋሳ ለአምቦ ውሃ ምንጭ የፒቪሲ እና የዲሲ አይ ቧንቧ ጨረታ ሂደትን በሚመለከት በዓለም አቀፍ ደረጃ የቻይና አምራች አሸናፊ ሆኖ ዕቃውን ጅቡቲ ወደብ ካደረሰ በኋላ ዕቃዎቹን ከጅቡቲ ወደ ፕሮጀክት ሥፍራው እራሱ ማድረስ ሲገባው የውሃ አገልግሎቱ እንደ አቅራቢው ሆኖ እንዲያጓጉዝ በማለቱ፣ የመጓጓዝ ሂደቱ ላይ የውሃው አገልግሎቱ ለማጓጓዝ ልምድ የሌለው በመሆኑ ማጓጓዝ በመዘግየቱ እና የመጡት ዕቃዎች ለ5 ወራት በጅቡቲ በመቆየታቸው ፕላስቲክ የሆኑት ፕሮጀክቱ ሥፍራ ከደረሱ እና ከተገጣጠሙ በኋላ በጸሃይ በመጎዳታቸውና በመፈንዳታቸው የውሃ አገልግሎቱ ከራሱ መደበኛ በጀት ከሀገር ውስጥ አምራቾች በመግዛት ለመተካት የተገደደ በመሆኑ ተጨማሪ 3.5 ሚሊዮን ብር ወጪ ያደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም

አቅራቢው በውሉ መሰረት እንዲያጓጉዝ አለመደረጉ እና ዕቃዎቹን ከወደብ በአፋጣኝ አንስቶ ወደ ውሃ አገልግሎቱ በማጓጓዝ ሂደት ውስጥ የሚ/ር መ/ቤቱ ክትትል፡ ድጋፍና በውሉ መሠረት ባልፈጸመው አቅራቢ ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉ፤

የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሁለገብ ድጋፍ አሰጣጥና የቴክኖሎጂ ሽግግር አፈጻጸምን በተመለከተ

120. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት በመስጠት ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠና ዓለም አቀፍ መስፈርትን ያሟላ ምርት ለሃገር ውስጥና ለዓለም ገበያ እንዲያቀርቡ ሊደግፍ ሲገባ ውጤታማ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት ባለመቻሉ በናሙና ከታዩት ሰባት ኤክስፖርት ቄራዎች በጥራት መጓደል ምክንያት በሶስት ዙር የቀረበ 270 ቶን (1.59 ሚሊዮን ዶላር ዋጋ ያለው) ሥጋ በመበላሸቱ ለ6 ቀናት ከገበያ የታገዱ መሆኑ፤

121. ኢንስቲትዩቱ የዳበረ ልምድ ካላቸው ሀገራት በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም፣ በሥጋ ሎጅስቲክስ አመራርና ግብይት ዙሪያ በእንስሳት ምርቶች ላይ የንግድ ትርኢቶችና ባዛሮችን በማዘጋጀት በገዥ ሀገራት በሚደረጉ መድረኮች ላይ በማስተዋወቅ እና በመዳረሻ ሃገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን እንዲሁም የሥጋ ፍላጎት፣ ዋጋና የተወዳዳሪ ሀገራት የምርት አቅርቦትን በመለየትና እንዲሟሉ በማድረግ ለማቀነባበሪያ ፋብሪካዎቹ ድጋፍ መስጠት ሲገባው አለመስጠቱ፤

122. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን አቅርቦት (የማሽኒያ፣ የኬሚካል፣ የላብራቶሪ መሳሪያዎች… እና የቁም እንስሳት አቅርቦት) እጥረት መንስኤዎችን በመለየት በአቅርቦት ዘርፍ ከተሰማሩ ባለሃብቶችና ተቋማት ጋር ለማስተሳሰር የሚያስችል የደሰሳ ጥናት (Supply chain study) በማካሄድ ተግባራዊ አለመደረጉና የእንስሳት አቅርቦትን ችግር ለመፍታት የግል ባለሃብቶችና የቄራ ባለቤቶች መሬት ወስደው የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል እንዲያረቡ እና እንዲያደልቡ ብሎም ከይዞታቸው ለእርድ እንዲያቀርቡ የእንስሳት እርባታ (ራንች)

እንዲያቋቁሙ አለመደረጉ እንዲሁም ለኤክስፖርት ቄራዎች እንስሳት የሚያቀርቡ ማህበራትና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችና ነጋዴዎችን በመለየት ከቄራዎች ጋር አለማስተሳሰሩ፤

123. በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎች ያልተዘጋጁና ያልተሰራጩ እንዲሁም ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሃብቶች ጠቋሚ ጥናት በማድረግ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል በማድረግ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ሊሰጥ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፤

124. ኢንስቲትዩቱ ከክልሎችና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየት ተገቢውን ውሳኔ እንዲያገኙ ሊያደርግ አለመቻሉ፤

<u>በሴቶች፤ ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የጉዲፈቻ ህፃናት መብትና ደህንነት አጠባበቅን በተመለከተ</u>

125. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህፃናት መብትና ደህንነትን የሚያስጠብቅ የመጨረሻ ረቂቅ ብሔራዊ የህፃናት ፖሊሲ አዘጋጅቶ በሚያዝያ 2003 ለሚመለከተው አካል ያቀረበ መሆኑ ቢታወቅም ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት እስከ 2008 ጊዜ ድረስ ፖሊሲው ያልፀደቀ መሆኑ፤

126. ሁሉም የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት የህፃናት አቀባበልና ምደባን በተመለከተ ወጥ የሆነ መመሪያ እና አሰራር ስርዓት ሊኖራቸው የሚገባ በመሆኑ ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡና ለችግር የተጋለጡ ህፃናት መምረጫ መመሪያ በሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የተዘጋጀና ህፃናትን በመምረጥ ሂደት ላይ መሳተፍ የሚኖርባቸው አካላት በግልፅ የተቀመጠ ቢሆንም በመመሪያው መሠረት የማይፈጸም መሆኑ፤

127. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ከ2004- 2007 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ በናሙና ተመርጠው በታዩት የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅቶች አማካኝነት ማለትም በአሜሪካ ወርልድ የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅት ወደ

አሜሪካ፣ በኩዊን ኦፍ ሜርሲ ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅት ወደ ፈረንሳይ፣ በቢታኒ ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅት ወደ አሜሪካ እና በአሶሴሽን ኦፍ መንዲ አዶፕታ ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅት አማካኝነት ወደ እስፔይን ጉብኝት ማድረጋቸው የተገለፀ ቢሆንም ኃላፊዎች በሄዱባቸው አገሮች ያገኙዋቸው በጉዲፈቻ ወደ ውጭ ሀገር የሄዱ ህፃናት ደህንነታቸው መጠበቁን እና የጉዲፈቻ ተጠቃሚ መሆናቸውን የጉብኝቱን ዝርዝር ሪፖርት ማቅረብ፤ እንዲሁም ባቀረቡት ሪፖርት መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድና ግብረ-መልስ ሊሰጡ የሚገባ ቢሆንም ይህ የማይፈጸም መሆኑ፤

128. በጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲ አማካኝነት ወደ ውጭ ሀገር ስለሄዱ ህፃናት የላከው ድርጅት /ጉዲፈቻ አስፈፃሚው/ በወር፣ በስድስት ወር፣ በዓመትና ህፃኑ 18 ዓመት እስኪሞላው ድረስ በሚቀጥሉት ተከታታይ ዓመታት በየዓመቱ ሪፖርቱን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መላክ የሚኖርበትና ጉዲፈቻ ስለተሰጡ ህፃናት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርበው ቅጂ ህፃኑ በጉዲፈቻ እንዲሄድ ለተደረገበት ክልል፣ የህፃናት ጉዳይ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች እና ህፃኑን ለሰጠው ማሳደጊያ ድርጅት ሊሰጣቸው/ሊደርሳቸው ሲገባ የማይደርስ መሆኑ፤

በንግድ ሚኒስቴር የገቢና ወጪ ዕቃዎች እና የህጋዊ ሥነ-ልክ ደረጃዎች ፍተሻ አፈፃፀምን በተመለከተ

129. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸው እንዲሁም የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት የሚወጡ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ፣ እንዲሁም ከውጪ የሚገቡ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት በጉምሩክ ጣቢያዎች ደህንነታቸውና ጥራታቸው እንዲሁም ተገቢውን መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውን ሊረጋገጥና ምርቶች የሀገሪቱን ህግና ደንብ ተከትለው መግባታቸውን/መለካታቸውን በማረጋገጥ ይሁንታ /Permit/ ሊሰጥ የሚገባ ቢሆንም አልፎ አልፎ የወጪ ምርቶች ከአገር ከመውጣታቸው በፊት ደህንነታቸው እና ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲሁም የሀገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት እንዲወጡ የማይደረግ መሆኑ፤

130. በአዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት የወጪና የገቢ ንግድ ዕቃዎች ተፈላጊውን የደረጃ መስፈርት የማያሟሉ ከሆነ የንግድ ዕቃዎቹ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ

ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማገድ እንደለበት የተደነገገ ቢሆንም በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የላብራቶሪ ውጤት ወይም በዓለም አቀፍ ሶስተኛ ወገን ሠርተፊኬት አምጥተው ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ደረጃቸውን የማያሚሉ መሆናቸው ተረጋግጦ እንዲታገዱ ከተደረገ በኋላ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጁ ከተደነገገው በተቃራኒ ደብዳቤ በመጻፍ እንዲለቀቁ የሚያደርግ መሆኑን፤

131. የኢትዮጵያ ደረጃ በሚያዘው መሰረት የተወሰዱ ናሙናዎች ከውጫዊ ተፅዕኖ ነጻ ሆነው የጥራት ባህሪያቸው ሳይለወጥ ከተወሰዱበት ሰዓት ጀምሮ በ48 ሰዓት ለፍተሻ ላብራቶሪ እንዲቀርቡ መደረግ ሲገባው እስከ አንድ ሳምንት ድረስ የሚቆዩ ከመሆኑም በላይ በላብራቶሪ ምርመራ ፈላጊዎች ቁጥር መብዛትና የላብራቶሪ ዕቃ መሣሪያ እጥረትና በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል በበቂ ሁኔታ ያለመኖር የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የደንበኞችን የላብራቶሪ የፍተሻ ውጤት መገለጽ ባለበት ጊዜና ሰዓት የማይገልጽ በመሆኑ አልፎ አልፎ ዕቃዎች የኢትዮጵያን አስገዳጅ ደረጃ ሳያሚሉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የሚለቀቁ መሆኑ፤

132. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ያላቸው ምርቶች አለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ኢንስፔክሽን አካላት የተረጋገጠ የላብራቶሪ ሰርተፊኬት ከአገልግሎት መጠየቂያ ጋር እንዲያቀርቡ ሊያደርግ፣ የሰርተፊኬቱ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ (Rondomly) አንድ ሶስተኛ ወካይ ናሙና ወስዶ ሰርተፊኬቱን ሊያረጋግጥና የሦስተኛ ወገን ሰርተፊኬት ማቅረብ ግዴታ መሆኑ ከሁለት ጊዜ በላይ ተነግሯቸው ሰርተፊኬት ማቅረብ ያልቻሉ አስመጪዎች ምርታቸው የደረጃ መስፈርት ማሟላቱ የላብራቶሪ ውጤት እስከሚገለጽ ድረስ በጉምሩክ እንዲቆይ መደረግ ሲኖርበት ለአንዳንድ ተገልጋዮች ከውጭ ለሚያስመጡት ዕቃ የሶስተኛ ወገን ሠርተፊኬት ሳያቀርቡ በነበረው አሰራር /በውዴታ ግዴታ/ እና የላብራቶሪ ውጤት ሳይገለጽ ምርቶች እየተለቀቁ መሆኑ፤

133. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጭ የሚገቡ የመለኪያ መሳሪያዎች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁና ትክክለኛ ስለመሆናቸው ሳይረጋገጥ

በጊዜያዊ መልቀቂያ የሚለቀቁና በክልሎችም የመለኪያ መሳሪያዎቹ ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን የማይረጋገጥ መሆኑ፤

በኢንቬስትመንት ኮሚሽን ለባለሀብቶች የሚሰጠው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ

134. በኮሚሽኑ የተለያዩ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ የዋሉ ቢሆንም የካፒታል ዕቃዎች ዝርዝር መመሪያ ባለመውጣቱ ለካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች የሚሰጡ ማበረታቻዎች በመጠን የተገደበ ባለመሆኑ ባለሀብቱ የጠየቀው ማበረታቻ በሙሉ የሚፈቀድበት ሁኔታ መኖሩ፣ በአስገብኚነት የስራ መስክ ላይም የተሰማሩ ከቀረጥ ነፃ ያስገቡትን እቃ ሲያከራዩ ማሳወቅ ቢኖርባቸውም የማያሳውቁ መሆኑን እና በማያሳውቁት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያደርግ የአፈፃፀም መመሪያ አለመኖሩ፣ በሌላ በኩል የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች የሚያከራዩ ባለሀብቶች እቃዎችን እንዴት እና በምን ሁኔታ ማከራየት እንዳለባቸው በዝርዝር የሚገልጽ መመሪያ ያልወጣ መሆኑ፣ በግብርና ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶችን ከማበረታታት አንፃር አሁን እየተሰራበት ያለው መመሪያ የባለሀብቶችን የመሬት ይዞታ ያላገናዘበ መሆኑ፣

135. በናሙና በታዩት በትግራይ፣ በኦሮሚያ፤ በአማራና በአዲስ አበባ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተጠየቁት መሣሪያዎች፣ ዕቃዎችና አክሴሰሪዎቻቸው ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱ አግባብነት ያላቸው ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ ተፈቅዶ እንዲገቡ መደረጉ፤

136. ማንኛውም ባለሀብት ለሚያቋቁመው አዲስ ድርጅት ወይም ነባር ድርጅቱን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ማስገባት እንደሚችል በደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ 13 ቁጥር አንድ ላይ ከተገለጸው ውጪ የኢንቨስትመንት ቦርድ የጉምሩክ የቀረጥ ነጻ እየፈቀደ መሆኑን፤

137. በኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ 13 ቁጥር 4 ላይ ኮሚሽኑ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ የሚፈቅድለት ማንኛውም ባለሀብት ዋጋቸው ከካፒታል እቃዎች ጠቅላላ ዋጋ 15 በመቶ የማይበልጡ መለዋወጫዎችን

ፕሮጀክቱ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት አመት ድረስ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ሊፈቅድ ይገባል ቢልም ኮሚሽኑ ከመመሪያ ውጭ ፕሮጀክቶች ማምረት ሳይጀምሩ እና ምን ያህል ማስገባት እንዳለባቸው /የመለዋወጫ ዕቃዎቹ የካፒታል ዕቃው 15 በመቶ መሆኑ ሳይረጋገጥ እየፈቀደ መሆኑ፤

138. ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጣ ማንኛውም ባለሀብት ስለኢንቨስትመንቱ የአፈፃፀም ሂደት በየሦስት ወሩ ሪፖርት እንዲያቀርብ ሊያደርግና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለተሰጣቸው ፕሮጀክቶች በሙሉ ዕቅድ አውጥቶ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የያዛቸው ሁኔታዎች መከበራቸውንና ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ሊከታተል የሚገባ ቢሆንም አብዛኛው ባለሀብት የአፈፃፀም ሪፖርት በየሦስት ወሩ እያቀረበ አይደለም እንዲሁም በኮሚሽኑም ሆነ በናሙና በታዩት በሁሉም ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ከቀረጥ ነፃ ማበረታቸውን የተሰጣቸው ባለሀብቶች ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው አላማ ውጪ ስለማዋላቸው ከአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ በስተቀር በዕቅድ ተይዞ ክትትል እየተደረገ አለመሆኑ

139. በናሙና በታዩት በሁሉም ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ከቀረጥ ነፃ ማበረታቸ የተሰጣቸው ባለሀብቶች ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው አላማ ውጪ ስለማዋላቸው ያለው ክትትል የላላ በመሆኑ ባለሀብቶች የወሰዱት ዕቃዎች በትክክል ለተፈቀደለት አለማ ያውሉት ወይም አያውሉት የማያውቁና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 279 በአንቀጽ 19 ቁጥር 3 መሠረት በተለያየ ምክንያት ኢንቨስትመንት ፍቃድ የተሰረዘባቸውን ባለሀብቶች ለይተው ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የማያሳውቁ መሆኑ፤

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የንብረት አስተዳደርና አወጋገድን በተመለከተ

140. የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአዲስ መልክ ሲቋቋሙ የነበራቸውን ንብረት ትክክለኛው ዋጋ በመነሻ ሂሳብ ሊይዙ የሚገባ ቢሆንም በናሙና ከታዩት ውስጥ በኮስቲክ ሶዳ አክስዮን ማህበር የመነሻ ካፒታሉ የተከፈለ ተብሎ በመመስረቻ ጽሑፍ ላይ ብር 68,899,000 ተብሎ የሠፈረ ቢሆንም በመዝገብ የተመዘገበው

ግን ብር 54,059,520 ብቻ መሆኑ እንዲሁም በእርሻ መሳሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ.ማ እንደ አዲስ በአክሲዮን ማህበር ሲቋቋም የነበረው የንብረት ዋጋ ብር 174,000,000 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 94,000,000 ንብረት አክሲዮን ማህበሩ መርጦ እንዲወስድ ከተደረገ በኋላ የተቀረው ለባለአደራ ቦርድ እንዲያስረክብ የታዘዘ ቢሆንም ባለአደራ ቦርድ ግን ንብረቱን የማስቀምጥበት መጋዘን የለኝም በሚል ምክንያት እስካሁን ለ13 ዓመታት ንብረቱን ሳይወስድ መቅረቱና ንብረቱም በዓይነት ተለይቶ ሳይመዘገብ ከመቆየቱም በላይ ለአደጋ በተጋለጠ ሁኔታ የሚገኝ መሆኑ፤ በተመሳሳይ ሁኔታ በሸበሌ ሆቴሎች አስተዳደር ሥር የነበረው የላንጋኖ ሎጅ ለፍል ውሃዎች አስተዳደር ሲተላለፍ የቋሚና አላቂ እቃዎች መነሻ ሂሳብ ሳይታወቅ የተላለፈ መሆኑና ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ የመነሻ ሂሳቡ የማይታወቅና በፍል ውሃዎች አስተዳደር የንብረት መዝገብ ያልተመዘገበ መሆኑን

141. የንብረት አስተዳደር ተግባርን የሚያከናውን የሥራ ክፍል የንብረቱ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎችን የንብረት ምዝገባ ካርድ ሊይዙ የሚገባ ቢሆንም በናሙና ከታዩት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች መካከል የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፣ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት እና የእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ.ማ ቋሚ ንብረቶች የት እና በማን እጅ እንዳሚገኙ ተመዝግበው ያልተያዙ መሆኑ፤

142. ቋሚም ሆነ አላቂ እቃ በተገቢው ሊጠበቁና ለተወሰነላቸው ዓላማና ተግባር ብቻ ሊውሉ የሚገባ ቢሆንም በናሙና ከታዩት ልማት ድርጅቶች ውስጥ በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት በርካታ ንብረቶች ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ የሚገኙ መሆናቸው፤ በግብርና ምርት ማሳደጊዎች አቅራቢ ድርጅት ንብረቶቹ ከዕቃ ግምጃ ቤት ወጪ ተደርገው ለሚፈለገው ስራ በትክክል ስለመዋላቸው የሚረጋገጥበት የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት የሌለ ከመሆኑም በላይ የታቀዱት ሥራዎች ተጠናቀው ንብረቶች ተርፈው ሲመለሱ ተመዝግበው ስለሚያዙበት ሁኔታ የቁጥጥር ስርዓት ባለመዘርጋቱና ንብረቶችን በሃላፊነት የሚረከባቸው አካል ባለመኖሩ በድርጅቱ ግቢ ውስጥ ፀሃይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው ተቀምጠው ለብልሽትና ብክነት በተጋለጠ ሁኔታ መገኘታቸው፤ በአትክልትና ፍራፍሬ ገበያ አ.ማ ከጣና በለስ ፕሮጀክት

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አማካኝነት በስጦታ የተገኘ ፊያት ኦኤም (OM) መለስተኛ የጭነት መኪና በሚቸልኮትስ ኩባንያ ለጥገና ጋራዥ ገብቶ አምስት አመት ያስቆጠረ (ታህሳስ 30, 2001 የገባ) በክትትል ማነስ እስከ ጥር 2006 ዓ.ም ድረስ ተጠግኖ ሳይወጣ የቆየ መሆኑና ሞተሩ (ቁጥር 336012 የሻንሲ ቁጥር 001597) የት እንደደረሰ የማይታወቅ መሆኑ፤

143. በናሙና ከታዩት የልማት ድርጅቶች በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት በኬሚካል ዕቃ ግምጃ ቤትና በተለያዩ መጋዘን ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውና ለብዙ ዓመታት የተቀመጠ ብዛቱ አምስት ባለ 200 ሊትር የሆነ ናይትሪክ አሲድ እና ሌሎች ኬሚካሎች (ሶዲየም ሃይድሮጅን ሰልፌት፣ አሴታማይድ፣ ቢስሙዝ፣ ትራይ ፖታሲየም ሳይትሬት እና ሜርኩሪ ኦክሳይድ) መኖራቸው፤

144. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈ ኬሚካሎች ለአርሶ አደሩ የሚሸጡ መሆናቸው ለምሳሌ አሲቲሊክ 2% ዲፒ ኤክስፓየር ዴት እ.ኤ.አ 2013 ብዛት 14,288.65 ኪሎ ግራም የአንዱ ዋጋ በ8.25 ጠቅላላ ዋጋ ብር 117,881.36 ዋጋ ያለው እና ከ2 ዓመት በፊት የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ ኬሚካል በድርጅቱ ሱቅ ውስጥ በመሸጥ ላይ መሆኑ እና 2.4 ዲ ኤክስፓየር ዴት 2 ወር ያለፈው ብዛት 3,702 ሊትር የአንዱ ዋጋ 76 ብር ጠቅላላ ዋጋ 281,352 ብር ዋጋ ያለው በድርጅቱ ሱቅ ውስጥ እየተሸጠ መሆኑ፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፉ ኬሚካሎች በድርጅቱ ግሪስ ዳማ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው ለምሳሌ 2,4D 2,353 ሊትር፣ ዶርስባን 206 ሊትር፣ አክቴሊክ 2% 14,288.45 ኪ.ግ፣ ማላታይን 118 ሊትር፣ ኢንዶሰልፋይን 407 ሊትር፣ ዲያዝኖን 23 ሊትር፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው በመጋቢት 2007 ዓ.ም ያለፈ ኬሚካሎች እስከ 06/01/2008 ዓ.ም ለአርሶ አደሩ ይሸጡ የነበሩ መሆናቸውና በድርጅቱ የሽያጭ መጋዝን ውስጥ ኦዲቱ እስከተከናወነበት ድረስ የነበሩ መሆናቸው፤

145. በአሰላ ብቅል ፋብሪካ ቀደም ብለው በፋብሪካው ለተለያየ አገልግሎት የተገዙ ኬሚካሎች ያለምንም አገልግሎት በመጋዝንና በላብራቶሪ ክፍል ለረዥም ጊዜ ተከማችተው መቀመጣቸው እና ኬሚካሎችን ለማስወገድ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር እንቅስቃሴ ቢኖርም ኬሚካሎቹ ሊወገዱ አለመቻላቸው፣ እንዲሁም

የኢትዮጵያ ልማት ማዕድን አ.ማ በካኦሊን ምርት ፊርጅ እና በቀንጢቻ ክሊኒኮች ውስጥ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ብዛት ያላቸው እና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው የተለያዩ መድሀኒቶች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

146. በመሆኑም ሁሉም የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች በኦዲቱ የታዩትን ክፍተቶች መነሻ በማድረግና መርሀ-ግብር በማዘጋጀት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ፣ በቀጣይም ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶችና ሌሎች ሥራዎች እንደመነሻ በመውሰድ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንደይከሰቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው አሳስበናል፡፡

የልዩ ኦዲት ስራዎች

147. በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በፍ/ቤቶች፣ በፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን፣ እንደዚሁም በሌሎች የተለያዩ አካላት ጥያቄ 6 የልዩ ኦዲት ስራዎች ተከናውኖ ሪፖርታቸው ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡

በመ/ቤታችን በተሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ

148. በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በጊዜ ገደብ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

149. በዚሁ መሠረት በ2007 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ወቅት በተደረገው የክትትል ኦዲት 38 መ/ቤቶች እና 11 ቅ/ጽ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ መሆናቸው ተረጋግጧል (ዝርዝሩን በአባሪ 3 ላይ ይመልከቱ)፡፡ እንዲሁም የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትን ጨምሮ ባለፉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት ሂሳባቸው የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት ወይም

አስተያየተ ሊሰጥበት ያልተቻሉ አሥራ አምስት መ/ቤቶች ትኩረት የሚያሻቸው በመሆኑ ዝርዝራቸው በአባሪ 4.ቀርቧል፡፡

150. በሌላ በኩል የ2007 ኦዲት እንደተጠናቀቀ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች የተገኙባቸው 99 መ/ቤቶች እና 12 የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች የማስተካከያ መርሃ-ግብር ነድፈው እንዲያሳውቁን ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ መርሀ-ግብሩን የላኩት 38 የፋይናንሻል ኦዲት እና 5 የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች ብቻ ናቸው፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ 2 ሀ እና ለ ላይ ይመልከቱ)

151. በተጨማሪም የማቋቋሚያ አዋጃችንን ድንጋጌ መነሻ በማድረግ ከ2002 እስከ 2006 በጀት ዓመታት ሂሳብ የኦዲት ግኝቶች ላይ የተወሰደውን እርምጃ በውስጥ ኦዲተሮቻቸው አረጋግጠው እንዲያሳውቁን ለ150 ባለበጀት መ/ቤቶች እና 84 ክዋኔ ኦዲት የተደረገባቸው መ/ቤቶች በደብዳቤ ተጠይቀው ከ150 መ/ቤቶች 102 (68%) ለክዋኔ ኦዲት ደግሞ 43 (51%) ብቻ ምላሻ ሰጥቷል፡፡ የእርምጃ አወሳሰድ ደረጃቸው ከ 0% እስከ 100% ይደርሳል፡፡ መ/ቤቶቹ ከሰጡት ምላሻ በእርምጃ አወሳሰድ ረገድ ላይ በርካታ ችግሮች የሚታዩ ስለሆነና የተወሰኑት በውስጥ ኦዲተሮቻቸውም አረጋግጠው ያልላኩ በመሆኑ ትንተና ተሠርቶ ወደ ፊት ራሱን የቻለ ሪፖርት ለተከበረው ም/ቤት የሚቀርብ ይሆናል፡፡

152. በአጠቃላይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እርምጃ የመውሰዱ ዝንባሌ ከዓመት ዓመት እየተሻሻለ ያለ ቢሆንም አሁንም እርምጃ ለመውሰድ የሚያንገራግሩ ወይም ፈቃደኛ ያልሆኑ መ/ቤቶችና ሀላፊዎች ከመኖራቸውም በላይ የተከበረው ም/ቤት ፊት ጭምር ቀርበው የዋና ኦዲተርን አስተያየት አንቀበልም የሚሉ አሉ፡፡ እነኚህ መ/ቤቶችና ሀላፊዎች ሊገነዘቡት የሚገባ ነገር ቢኖር ያለበቂ ምክንያት በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በቀረቡ የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሣቦች ላይ በወቅቱ እርምጃ ያለመውሰድ የሕግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑንም ጭምር ነው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት የማስተካከያ እርምጃ በፍጥነት ሊወስድ ይገባል፡፡ ም/ቤቱም በዚህ ረገድ እያደረገ ያለውን ጠንካራ

ክትትልና ቁጥጥር የበለጠ ሊያጠብቅና ተገቢውን እርምጃ ጭምር ሊወስድ ይገባል፡፡

የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ

153. የለውጥ ሥራ አተገባበር በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ሪፖርቱ በሚሸፍነው ጊዜ በዋንኛነት ከተከናወኑት ዓበይት ተግባራት መካከል ዋንኞቹ የውጤት ተኮር ሥርዓትን ለመተግበር በሁሉም የሥራ ክፍሎች የካስኬድንግ ሥራ ማጠናቀቅ፣ ውጤት ተኮር ሥርዓትን መሠረት ያደረገ ስትራቴጅክ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ይህንኑ ስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት ያደረገ ዓመታዊ ዕቅድ ማዘጋጀትና ከመጋቢት 2008 ጀምሮ የተከናወኑ ተግባራትን በውጤት ተኮር የምዘና ሥርዓት መሠረት ለመመዘን ዝግጅቶች ተጠናቅቋል፡፡ በተጨማሪም የለውጥ ሥራዉን ለመምራትና ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል የሰው ሀይል ለስራ ክፍሉ እንዲሟላ ተደርጎ ሥራው በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

154. በሌላ በኩል የመ/ቤታችን የመልካም አስተዳደር ችግሮች፣ መንስዔያቸውና መፍትሄዎቹ ሁሉንም የመ/ቤቱን ሠራተኛ ባሰተፈ መንገድ በዝርዝር በመለየት የአፈጻጸም መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ በታቀደው መሠረት ሥራዎቹ በመከናወን ላይ ናቸው፡፡

ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ

155. በዚህ ረገድ ሥራዎችን ተቋሚዊ ለማድረግ ታስቦ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ የሚከታተሉ ሀላፊና ባለሙያ ተመድበው ሥራዎቹን በቋሚነት በማከናወን ላይ ናቸው፡፡ በተለይ ሴቶች የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ ስለመሆናቸው ኦዲት በምናደርጋቸው መ/ቤቶች ሁሉ ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ የ2008/09 የኦዲት እቅድ አካል ተደርጎ በመፈጸም ላይ ይገኛል፡፡ እንደዚሁም ቀደም ሲል ተጀምሮ የነበረው በየሁለት ወሩ ግማሽ ቀን የሚደረገው የመ/ቤታችን ሴት ሰራተኞች ቋሚ የጋራ የምክክርና የልምድ መለዋወጫ መድረክ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

156. የHIV/AIDS ሥራ አሁንም እየተሠራ ያለው በፈቃደኛ መ/ቤቱ ሠራተኞች ሲሆን በመደቡ ላይ ቋሚ ሠራተኛ መድቦ ባለቤት ኖሮት እንዲሠራ እስከአሁን

የተደረገው ጥራት ባይሳካም በቅርቡ መፍትሄ እንደሚያገኝ ይጠበቃል፡፡ እስከዚያው ግን የ HIV/AIDS ቀን የማክበር፤ በስራ ቦታ HIV/AIDS የመከላከል እንዲሁም የግንዛቤ መፍጠሪያ ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ

157. ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ለኦዲት ባለሙያ 645 እና ለድጋፍ ሰጪ 314 በድምሩ 959 ሲሆን፣ በየካቲት ወር 2007 የኦዲት ሥራው ሲጀመር የነበረው የሰው ሀይል 260 ኦዲተሮችና 139 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 399 ነበር፡፡ በኦዲት ዓመቱ 59 ኦዲተሮችና 27 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በድምሩ 86 ሠራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን፣ ከድጋፍ 1 እና ከኦዲት 3 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ፣ 1 በሞት የተለዩ 3 በዲሲፒሊን ቅጣት፣ 42 ኦዲተሮችና 20 ድጋፍ ሰጪ በድምሩ 62 ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ መ/ቤቱን የለቀቁ ሲሆን በአጠቃላይ በኦዲት ዓመቱ 71 ሰው ኃይል ከመ/ቤቱ ለቀዋል፡፡

158. በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ የኦዲት ባለሙያዎች 173 ወንዶችና 95 ሴቶች በድምሩ 268፣ የድጋፍ ሰጪ 69 ወንዶችና 76 ሴቶች በድምሩ 145 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በአጠቃላይ 413 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን፣ 546 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ እነኚህ ክፍት የሥራ መደቦችን ለመሙላት በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

የ2007 በጀት ዓመትና 2008 በጀት ዓመት

የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም

159. በ2007 በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ ብር 27,732,088.47 በጀት ተፈቅዶ ብር 24,344,092.35 ወይም 87.78% ሥራ ላይ የዋለና ያልተሰራበት ብር 3,387,996.12 (12.12%) የነበረ ሲሆን፣ ለ2008 በጀት ዓመት ዕቅድ ማስፈጸሚያ ለመ/ቤታችን ከተፈቀደው ብር 42,059,628.46 ውስጥ እስከ መጋቢት 30/2007 የነበረው የዘጠኝ ወር በጀት

ብር 31,544,721.35 በመሆኑ፣ አፈፃፀሙ ደግሞ ብር 27,833,974.74 ወይም 88.24% ሆኗል፡፡

መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች

160. መ/ቤታችን በሕገ-መንግሥትና የማቋቋሚያ አዋጁ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ቢሆንም በሥራ ሂደት እየተፈታተኑን ከሚገኙ ተግዳሮቶች መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

161. ዋናው የመ/ቤታችንና የሥራችን ተግዳሮት የነበረው ከፍተኛ የሠራተኛ ፍልሰት ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የተሻለ ዕውቀትና ክህሎት የነበረው ሠራተኛ እስከ ህዳር 2008 በከፍተኛ ደረጃ ይፈልስ ስለነበር የኦዲትም ሆነ ሌሎች የመ/ቤቱ ሥራዎች በታቀደው ጊዜና ፍጥነት እንዲሁም ጥራት እንዳይከናወን አድርጓል፡፡ ይሁንና መንግሥት መ/ቤቱ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሁም መልካም አስተዳደር ከማስፈን አንፃር የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ከግምት ውስጥ በማስገበት ከህዳር 2008 ጀምሮ የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ማሻሻያ በመደረጉ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ መረጋጋት ከመፈጠሩም በላይ ሊፈርስ የነበረው ተቋም እንዲያንሰራራና የሠራተኛውም ተነሳሽነት እንዲጨምር አድርጓል፡፡ ለዚህም በሠራተኛውና በራሴ ስም ለተከበሩ አፈ ገባዔና መላው የም/ቤት አባላት እንዲሁም ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

162. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ መሠረት ሁሉም መ/ቤቶች ሂሳባቸውን የበጀት ዓመቱ እንዳለቀ እስከ መስከረም 30 ሂሳባችን ዘግተው ለኦዲት ማቅረብ ቢኖርባቸውም 64 መ/ቤቶች ወይም 44.13% (ዝርዝሩን በአባሪ 1 ይመልከቱ) የሚሆኑት ሂሳባችውን ከመስከረም 30/2007 በኋላ ከጥቅምት1/2008 እስከ ሚያዝያ 3/2008 ድረስ አዘግይተው ለኦዲት ያቀረቡ በመሆኑ የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በታሰበው ጊዜ ማጠናቀቅ አለስቻለንም፡፡ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ሂሳቡን ዘግተናል ብለው ከሰጡን መ/ቤቶችም ውስጥ የማይናቅ ቁጥር ያላቸው አልዘጉም ተብሎ ስማቸው እንዳይነሣ እንጂ መረጃዎችን በሚገባ አሟልተው ባለመሆኑ በዚህ ዓመት ብሶበት የመጣ ሌላው ችግር ነው፡፡ በዚህ ዓመት ችግሩን አስታምመን ሥራችንን ከዳር ለማድረስ

ጥረት ያደረግን ቢሆንም ለወደፊቱ የዚህ ዓይነቱ አሠራር የማያዋጣ በመሆኑ መ/ቤቶች አሠራራቸውን ሊያሻሽሉ ይገባል፡፡

163. ለኦዲቱ ሥራ የሚደረገው ትብብር ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል ያሳየ ቢሆንም አልፎ አልፎ አሁንም ያለመተባበር (በወቅቱ የሥራ ቦታ ያለማመቻቸትና መረጃ ያለመስጠት፣ የሂሳብ መግጫ ሪፖርታቸውን በሕግ በተደነገገው ጊዜ አዘጋጅተው ለኢዲት አለማቅረብና አንዳንዴም ዘግይቶ የቀረበውን እንደገና ማስተካከያ አድርገናል በማለት ኦዲተሮቹን ለተጨማሪ ስራና ማጣራት ጊዜያቸው እንዲባክን ምክንያት መሆን፣ ኦዲተሮች ሥራቸውን አጠናቀው የመውጫ ስብሰባ አድርገው ከወጡና ወደ ሌላ ሥራ ከተሰማሩ በኃላ በኦዲት ወቅት ያላቀረቡትን ማስረጃዎች አሉን በማለት መ/ቤታችን ድረስ ይዘው የማምጣት፣ በመጀመሪያው የመውጫ ስብሰባ ላይ ባለመገኘት ድጋሚ እንዲደረግ መጠየቅ) ችግሮች የሚታይ በመሆኑ መ/ቤቶቹ በፍጥነት እነኚህን ችግሮች በማስወገድ ሕጋዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

164. የተወሰነ መሻሻል የሚታይ ቢሆንም በርካታ ኦዲት ተደራጊዎች ከመ/ቤታችን በሚላኩ የስራ አመራር ሪፖርቶች ላይ በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠትና በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሠረትም በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ የማስተካከያ እርምጃ ያለመውሰድና ካለፈው ስህተት ባለመማር ተደጋጋሚ የሕግ ጥሰቶችን የመፈጸሙ ችግሮች አሁንም የቀጠሉ ናቸው፡፡

<u>የ2008/9 ኦዲት ዓመት ዕቅድ</u>

165. ለሰው ሀይል ፍሰቱ ምክንያት መንስዔ የሆነው ችግር በመቀረፉና ክፍት የሥራ መደቦቹ እንደሚሟሉ ታሳቢ በማድረግ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሽፋን 100% ሆኖ እንዲቀጥል 171 ባለበጀት መ/ቤቶችን የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ለማድረግ ታቅዷል፡፡ ካለፉት ዓመታት በተለየ ሁኔታ የኦዲት ጥራት የሁሉም ኦዲት ፈፃሚ ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ ተደርጎ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ ተነድፏል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከመጋቢት 2008 እስከ ጥር 2009 ድረስ 20 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችንና 6 የክትትል ኦዲት በማከናወን 26 ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዷል፡፡ በሌላ በኩል ከመጋቢት 2008 እስከ ጥር 2009 ድረስ በ305 የመሠረታዊ አገልግሎት

ተጠቃሚ በሆኑ ወረዳዎችና የሴክተር ቢሮዎች የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ ለማከናወን እንደዚሁም አንድ ፕሮግራም አቀፍ ኦዲት በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ደረጃ ለማካሄድ በእቅድ ተይዟል፡፡

166. በዚሁ መሠረት ከመጋቢት 5 እስከ መጋቢት 30/2008 ባለው ጊዜ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በ46 መ/ቤቶች እና 8 የገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ደግሞ ካለፈው ዓመት የዞሩ 1 ጨምሮ 8 የክዋኔ ኦዲቶች እና 26 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲቶች ተጀምረው በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ከመሆኑም በላይ በአጠቃላይ የኦዲቱ ሥራ እስከ አሁን በታቀደው መሠረት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

<u>በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት</u>

167. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ኃላፊነት ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሳቦችን በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽኑ እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት አስደርጎ በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት አስፈላጊው የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊ ድርጅቶች፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በደብዳቤ አስፈላጊው ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

168. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በ2007 በተከናወኑ ኦዲቶች የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 2 ክፍል 3 በዝርዝር የቀረበ ስለሆነ ዝርዝሩን ከዚያው መመልከት ይቻላል፡፡

<u>ኦዲት የተደረጉ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የሂሣብ መግለጫዎች ላይ የተሰጠ ኦዲት አስተያየት</u>

169. በ2007 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 89 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በውጭ

መንግሥታት የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሣብ ደግሞ 168 በድምሩ 257 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገው መ/ቤት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን ብቻ እንደ አንድ በመቁጠር የተወሰደ ነው) ኦዲቶች ተከናውኗል፡፡

170. በእነዚህ ሪፖርቶች ላይ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ዓይነት ሲተነተን፤ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት 164፣ ነቀፌታ ያለበት አስተያየት 77፣ አቋም የማይወሰድበት አስተያየት 14፣ አጥጋቢ ሆነው ባለመገኘታቸው የተቀውሞ አስተያየት የተሰጠበት 1 እና አስተያየት ያልተሰጠበት ልዩ ኦዲት 1 በድምሩ 257 ናቸው፡፡

171. በሌላም በኩል መ/ቤታችን ባለው መረጃ መሠረት ከሁለት ዓመታት በላይ ሂሣባቸውን ዘግተው ኦዲት ያላስደረጉ 22 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይገኛሉ፡፡

የኮርፖሬሽኑ የዕቅድ ክንውን

172. በ2007 በጀት ዓመት መጀመሪያ በነበረው 143 (99 ኦዲተሮችና 44 ድጋፍ ሰጪ) የሰው ኃይል 242 ኦዲቶችን ለማከናወን አቅዶ 248 ኦዲቶችን ወይም ከዕቅዱ በላይ 6 (2%) ለመፈጸም ችሏል፡

የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

173. ኮርፖሬሽኑ በ2007 በጀት ዓመት ከኦዲት ሥራ አገልግሎት ብር 23,842,639.00 ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር 26,595,579.00 ገቢ አግኝቷል፡፡ በሌላም በኩል ብር 19,962,911.00 ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር 19,290,996.00 ወጪ ያደረገ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ ብር 5,335,543.00 የተጣራ ትርፍ ሊያገኝ ችሏል፡፡

ማጠቃለያ

174. በሪፖርቱ እንደተመለከተው በ2007 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው ኦዲት በሂሳብ ምርመራ ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የተያዙትን ጨምሮ የኦዲት ሽፋኑን 100.00% ደርሷል፡፡ የፋይናንስና ሕጋዊነት የኦዲት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ የአዲስ አበባ የኒቨርሲቲ የ2007 ሂሳብ ኦዲት የተጠናቀቀና የስራ

አመራር ሪፖርት የተላከ ቢሆንም የመውጫ ስብሰባ ተደርጎ የመጨረሻ ሪፖርት ወጪ ባለመሆኑ የዕቅድ ክንውናችን 99.31% ሆኗል፡፡

175. የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ 19 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችና 4 የክትትል ኦዲቶች በድምሩ 23 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ለማውጣት ታቅዶ 22 ሪፖርቶች (95.65%) ወጪ የሆኑ ሲሆን ቀሪው አንድ ኦዲትም ሥራው ተጠናቅቆ የመውጫ ስብሰባ ብቻ ባለመደረጉ ሪፖርቱ ወጪ አልሆነም፡፡

176. የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ኦዲትን በተመለከተ በ300 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች ኦዲቱን ለማከናወን ታቅዶ በ294 (98.00%) ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

177. ውዝፍ የኦዲት ሥራ አለመኖሩና ሁሉንም የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶችን በየዓመቱ ኦዲት በምናደርግበት ደረጃ ላይ መገኘታችን የአሠራር ክፍተቶችን በፍጥነት በመለየት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ዕድል የሚሰጠን ቢሆንም፤ በተደጋጋሚ የሚታዩ ተመሳሳይ ነገር ግን ትኩረት ቢሰጣቸው ኖሮ ሊወገዱ የሚችሉ ግድፈቶች በዚህም ዓመት ማስቀረት አለመቻሉ አሁንም የቱን ያህል ትኩረት ለዚህ ጉዳይ ሊሰጥ እንደሚገባ አመላካች ነው፡፡ ስለሆነም የሚመለከታቸው ሁሉ የተጠናከረ ክትትል ሊያደርጉና ተገቢውን እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡ ዝርዝር የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቱ በሁለት ጥራዝ እንደዚሁም የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርት ደግሞ በ21 ጥራዝ ተዘጋጅቶ ለተከበሩ አፈ-ጉባዔ የተላከ በመሆኑ ሪፖርቶቹን በም/ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ቋሚ ኮሚቴዎች ጭምር በጥልቀት ተመርምሮ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

178. እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ አሁንም እየተንከባለሉ የመጡት ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች፣ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ በየዓመቱ የሚታዩ ተደጋጋሚ ችግሮችና ከውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ አጠቃቀምና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ

ችግሮች፣ እንደዚሁም በመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች ሊታረሙና ሊስተካከሉ አልቻሉም፡፡

179. በሌላ በኩል ከመንግሥት ግንባታዎች ጋር በተያያዘ በወቅቱና በተያዘላቸው በጀት ያለመጠናቀቅ፣ መፍትሔ ሣያገኙ ለረጅም ወራትና ዓመታት ጭምር የግንባታ ሂደታቸው የቆሙ ፕሮጀክቶች አፋጣኝ እርምጃ የሚያሻው በመሆኑ አሁንም በሚመለከተው ሁሉ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፣፣

180. መሻሻል ሲገባው አሁንም ያልተሻሻለው የባለበጀት መ/ቤቶች ሂሳብን በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ ዘግቶ ለኦዲት ያለማቅረብ ጉዳይ በአንክሮ ሊታይና ተገቢው እርምጃ የሚያሻው ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በእኛ በኩል ጉዳዩን በማስታመም ኦዲቱን ለማጠናቀቅ ጥረት እያደረግን ቢሆንም ሁኔታው ሊቀጥል ስለማይገባ በም/ቤቱም ሆነ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በኩል ሊታይና አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

181. የሥራ ቦታ ችግራችንን ለማቃለል መንግስት ትኩረት ሰጥቶ ደረጃውን የጠበቀ ህንፃ ስላስገነባልንና ከፍተኛና እጅግ ፈታኝ ችግር ሆኖ የቆየውን የሠራተኛ ፍልሰት ችግር ለማቃለል ከህዳር ወር/2008 ጀምሮ በመንግስት ለመ/ቤቱ የተፈቀደው የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ጭማሪ ባለው ሠራተኛ ዘንድ ከፍተኛ መነቃቃት የፈጠረና ከገበያም ለመሳብ ከዚያ ወዲህ ባወጣነው የስራ ማስታወቂያዎች ተስፋ የጫረ በመሆኑ ለተከበሩ አፈ ገባዔና መላው የም/ቤት አባላት እንዲሁም ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በድጋሚ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

182. በመጨረሻም የሚደረገው ኦዲት የአሠራር ክፍተቶችን በማረም ተጠያቂነትንና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ የበለጠ አስተዋፅኦ እንዲያደርግና እሴት እንዲጨምር በኦዲት ማሻሻያ አስተያየቶች መሠረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ሁሉም የሚመለከተው አካል ተገቢውን ግፊትና ክትትል እንዲያደርግ በድጋሚ እየጠየቅኩ በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

ሂሳባቸውን በወቅቱ ያልዘጉና ዘግይተው ለኦዲት ያቀረቡ መ/ቤቶች

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
		የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	
1	1	የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ	20/02/2008
2	2	የወለጋ ዩኒቨርስቲ	30/02/2008
3	3	የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	17/02/2008
4	4	የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ	11/2/2008
5	5	የመንግስት የፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ	17/02/2008
6	6	የፕሬዚደንት ጽ/ቤት	15/02/2007
7	7	የፌዴሬሽን ምክር ቤት	2/2/2008
8	8	የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር	26/02/2008
9	9	የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን	11/02/2008
10	10	የድሬደዋ ዩኒቨርስቲ	26/04/2008
11	11	የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት	29/02/2008
12	12	የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት	8/03/2008
13	13	የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር /በጀት ሂሳብ 2007/	20/05/2008
14	14	የደብረ ብርሀን ዩኒቨርስቲ	25/04/2008
15	15	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	3/8/2008
		የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	
16	1	የቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር	5/4/2008
17	2	የቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር	2/2/2008
18	3	የቀድሞው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	17/03/08
19	4	የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	8/2/2008
20	5	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	22/04/08
21	6	የሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	5/4/2008
22	7	የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	3/2/2008
23	8	የውሃ ቴክኖሎጂ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት	11/2/2008
24	9	የምግብ መጠጥና ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	23/02/08
		የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	
25	1	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	29/02/08
26	2	ሐዋሳ ዩኒቨርስቲ	24/05/08
27	3	ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ	22/03/08

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
28	4	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	25/04/08
29	5	አዳማ ዩኒቨርሲቲ	18/05/08
30	6	ዲላ ዩኒቨርስቲ	7/3/2008
31	7	አክሱም ዩኒቨርሲቲ	10/5/2008
32	8	ወሎ ዩኒቨርስቲ	29/02/08
33	9	አድግራት ዩኒቨርሲቲ	3/2/2008
34	10	መደወላቡ ዩኒቨርስቲ	4/2/2007
35	11	ወልድያ ዩኒቨርሲቲ	12/2/2028
36	12	ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ	3/4/2008
37	13	ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ	6/5/2008
38	14	አገር አቀፍ የትም.ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ	16/05/08
39	15	ቴ/ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ	28/03/08
40	16	ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር	ታህሳስ/2008
41	17	ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል	6/2/08
42	18	ቡሌ-ሆራ ዩኒቨርስቲ	17/02/08
		የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	
43	1	ፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	10/3/2008
44	2	የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉደዮች ሚኒስቴር	19/04/08
45	3	የሰነዶች ምዝገባና መረጋገጫ ጽ/ቤት	2/2/2008
46	4	የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ	15/2/08
47	5	ንግድ ሚኒስቴር	25/4/08
48	6	የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ	29/3/08
49	7	የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት	12/2/2008
50	8	የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል	7/3/2008
51	9	የፌዴራል የከተማ መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ	7/4/2008
52	10	የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን	1/2/2008
53	11	የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	3/2/2008
54	12	የኢትዮጵያ ብሓራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት	6/3/2008
55	13	የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት	12/4/2008
56	14	የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	21/03/08
57	15	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ	16/03/08
58	16	የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ	9/3/2008
59	17	የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	24/02/2008
60	18	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	20/03/2008

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
61	19	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	23/03/2008
62	20	የቀድሞው የፕራይቬይታዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ	3/3/2008
63	21	የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	15/02/2008
64	22	የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲቲዩት	4/2/2008

አባሪ 2

ሀ/ የ2007 ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት የመርሃ ግብር እስከ ሚያዝያ 25 የላኩ እና ያልላኩ መ/ቤቶች ዝርዝር

ተራ ቁጥር	የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
1	የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	x	
2	የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል	x	
3	የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ሚ/ር	x	
4	የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዩች ጽ/ቤት	x	
5	ሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል	x	
6	የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	x	
7	የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ	x	
8	ቤተመንግሥት አስተዳደር	x	
9	ጂግጂጋ ዩኒቨርሲቲ	x	
10	አምቦ ዩኒቨርሲቲ	x	
11	የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት	x	
12	ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	x	
13	ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	x	
14	ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት	x	
15	የኢትዩ. ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት	x	
16	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	x	
17	ትራንስፖርት ሚኒስቴር	x	
18	ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ	x	
19	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	x	

ተራ ቁጥር	የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
20	ወሎ ዩኒቨርሲቲ	x	
21	የኢት. ምግብ መድሃኒት የጤና ክብካቤ	x	
22	የበጉ አድራጐት ድረጅቶችና ማሕበራት ኤጀንሲ	x	
23	የኢትዮ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	x	
24	የመንግሥት ግዥ ንብረት ማስወገድ	x	
25	ብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	x	
26	መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	x	
27	የኘሬዝዳንት ጽ/ቤት	x	
28	የፌዴራል ጉዳዮችና የአርብቶ አደሮች አካባቢ ልማት ሚ/ር	x	
29	ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት	x	
30	ዲላ ዩኒቨርሲቲ	x	
31	ሲቪል ሰርቪሲ ዩኒቨርሲቲ	x	
32	ብሄራዊ ቤተመዘግብትና ቤተ መጽሐፍት	x	
33	የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን	x	
34	የመንግስት የፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ	x	
35	ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ	x	
36	የማዕድን፣ የነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር	x	
37	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	x	
38	የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን	x	
39	የማዕከላዊ ስታቲክስ ኤጀንሲ		x
40	የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን		x
41	ወለጋ ዩኒቨርስቲ		x
42	ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ		x
43	የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር		x

ተራ ቁጥር	የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
44	የኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል		x
45	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር		x
46	የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር		x
47	የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን		x
48	የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ		x
49	የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት		x
50	የመንግስት ልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ		x
51	የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት		x
52	የደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲ		x
53	የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ		x
54	የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት		x
55	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን		x
56	የፍትህ ሚኒስቴር		x
57	የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን		x
58	የሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔ ጽ/ቤት		x
59	የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ		x
60	የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም		x
61	አ.አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ		x
62	አዳማ ዩኒቨርሲቲ		x
63	ጎንደር ዩኒቨርስቲ		x
64	ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ		x
65	ሳይንስና ቴክሎኖጂ ሚኒስቴር		x
66	የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት		x
67	ጅማ ዩኒቨርሲቲ		x

ተራ ቁጥር	የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
68	አገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ		x
69	ሚዛን ዩኒቨርሲቲ		x
70	ከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ		x
71	አዲግራት ዩኒቨርሲቲ		x
72	አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ		x
73	አሶሳ ዩኒቨርሲቲ		x
74	መቱ ዩኒቨርሲቲ		x
75	አክሱም ዩኒቨርሲቲ		x
76	ሰመራ ዩኒቨርሲቲ		x
77	ወላይታ ዩኒቨርሲቲ		x
78	ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ		x
79	ወልዲያ ዩኒቨርስቲ		x
80	የፌ/ቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ኤጀንሲ		x
81	ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ		x
82	የፌ/ቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና ኢንስቲትዩት		x
83	ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ		x
84	ትምህርት ሚኒስቴር		x
85	የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር		x
86	የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት		x
87	የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል		x
88	የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢኒስቲትዩት		x
89	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን		x
90	የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ		x
91	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን		x

ተራ ቁጥር	የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
92	የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን		x
93	የአካባቢ፣ ደንና የአየር ለውጥ ሚኒስቴር		x
94	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ		x
95	የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን		x
96	የምግብ መጠጥና ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት		x
97	የስምጥ ሸለቆ ሃይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን		x
98	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን		x
99	የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር		x

ለ/ የ2007 በጀት ዓመት የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የመርሃ ግብር እስከ ሚያዝያ 25 የላኩ እና ያልላኩ መ/ቤቶች ዝርዝር

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
1.	የሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር	x	
2.	የፌደራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ	x	
3.	የፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ	x	
4.	የኢትዮ እግር ኳስ ፌደሬሽን	x	
5.	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን	x	
6.	የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ		x
7.	የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ		x
8.	በመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ		x
9.	ፍትህ ሚኒስቴር እና የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር		x
10.	የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር		x
11.	የኢትዮጵያ ኢንቨሲትመንት ኮሚሽን		x
12.	የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር		x

አባሪ 3

ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት በተወሰኑ ነጥቦች ላይ

እርምጃ ያልወሰዱ መ/ቤቶች

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	በጀት ዓመት
		የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	2006
1	1	በውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት	X
2	2	የኢትዮጵያ ዱር እንሰሳት ጥበቃ ባለሥልጣን	X
3	3	በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	X
4	4	የህብረት ሥራ ኤጀንሲ	X
5	5	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	X
6	6	የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን	X
7	7	የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት	X
8	8	በእንሰሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን	X
9	9	በአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	X
10	10	በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	X
11	11	በቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር	X
12	12	የብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት	X
13	13	በአለርት ማዕከል	X
14	14	በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	X
15	15	በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	X
		የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	X
16	1	ገቢዎችና ጉምሩክ በዋናው መስሪያ ቤት	X
	1.1	በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት	X
	1.2	በጅማ ቅ/ጽ/ቤት	X
	1.3	በኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት	X
	1.4	ድሬ ዳዋ ቅ/ጽ/ቤት	X
	1.5	በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት	X
	1.6	ምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	X
	1.7	በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት	X
	1.8	በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በኩል	X
	1.9	በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት	X

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	በጀት ዓመት
	1.10	ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	X
		አቅም ግንባታ መ/ቤቶች	X
17	1	በአዲግራት ዩኒቨርስቲ	X
18	2	በአክሱም ዩኒቨርሲቲ	X
19	3	በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ	X
20	4	በወልድያ ዩኒቨርሲቲ	X
21	5	በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	X
22	6	በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ	X
23	7	በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	X
24	8	በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ	X
25	9	በደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ	X
26	10	አሶሳ ዩኒቨርስቲ	X
27	11	ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ	X
28	12	ጅማ ዩኒቨርስቲ	X
29	13	መቱ ዩኒቨርስቲ	X
30	14	ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ	X
31	15	ሠመራ ዩኒቨርስቲ	X
		ንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	X
32	1	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	X
33	2	የአገር መከላከያ የሚኒሰቴር	X
34	3	የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ	X
35	4	የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	X
36	5	ንግድ ሚኒስቴር ሚኒስቴር	X
37	6	የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	X
38	7	የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	X

ባለፉት ተከታታይ ሶስት ኦዲቶች ሂሣባቸው የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው /X/ ወይም አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች /XX/

ተ.ቁ		የመ/ቤት ስም	በጀት ዓመት		
			2007	2006	2005
		የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች			
1	1	የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ	X	XX	X
2	2	የገቢዎችና ጉምሩክ ባላስልጣን	X	X	X
		የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች			
3	1	የቀድሞው ግብርና ሚኒስቴር	X	X	X
		የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች			
4	1	ወሎ ዩኒቨርስቲ	X	XX	X
5	2	አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	X	X	XX
6	3	ጎንደር ዩኒቨርስቲ	X	X	X
7	4	ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ	X	X	XX
8	5	ጅማ ዩኒቨርስቲ	X	X	X
9	6	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ	X	X	XX
10	7	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
11	8	ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ	X	XX	XX
12	9	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	X	X	XX
13	10	ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
		የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች			
14	1	የአገር መከላከያ ሚኒስቴር	XX	XX	XX
15	2	የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	XX	X	X